ክርስቲያናዊ ሕይወትን መኖር

Living the Christina Life

Albert N. Martin
ትርጉም በዘመን እንዳለ

ክርስቲያናዊ ሕይወትን

መኖር

በአልበርት ማርቲን

ትርጉም በዘመን እንዳለ

Living the Christina Life

Albert N. Martin

Copyright © **The Banner of Truth Trust 1991**

Originally published in English under the title Living the Christian Life

By the Banner of Truth Trust, Edinburgh EH12 6EL,UK

All rights reserved.

Translated and printed by MERF-ETH TEAM, 2021

+251911790701

email : zemendale@gmail.com

እንደ ክርስቲያን መኖር ያለብኝ እንዴት ነው? ይህ የላቀ ጠቀሜታ ያለው ጥያቄ ነው፡፡ በክርስቶስ ኢየሱስ ያለኝ ሕይወት እና ክርስቲያናዊ ሕይወቴን እንዴት መኖር እንደሚገባኝ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረቶች ላይ መመሥረቴ አንድ እርግጠኛ ልሆንበት የሚያስፈልግ ጉዳይ ነው፡፡ የክርስቲያናዊ ሕይወት ዋና ዋና መሮሆዎችን ለአንባቢያን ለማስፈር ሳስብ ወቅት ሦስት ዋና ምክንያቶችን ይዤ ነው፤

ነኛ. የመጽሐፍ ቅዱሳዊውን ሥነ-መለኮታዊ ክርስቲያዊ ኑሮ ረቂቅ ብጽፍ እመኛለሁ፡፡ ዓላማዬም ምርጥ በሆነ እና መጽሐፍቅዱሳዊ ለዛው እንደያዘ ያለሃፍረት ማስረጽ ነው፡፡

2ኛ. እንደ ክትባት ብከትባቸሁና ለዋና ዋናዎቹ በክርስትና ላይ ለሚነሱ የሐሰት ትምህርቶች ባነቃችሁ - ባዘጋጃችሁ - ባስታጥቃችሁም እመኛለሁ፡፡ አንዳንዶቻችን እንዲህ ካለው ትምህርት ጋር በክርስትናችን የመጀመሪያዎቹ ወራት ፈጥነን ተዋውቀን በሆነ ብለን እናስባለን፡፡ ፈጽሞ ልንይዛቸው የማንችላቸውን ጥንቸሎች በማራወጥ የበዙ ዓመቶቻችንን አባከንናቸው፡፡ እንደ ክርስትያን የመኖርን ትርጉም ለማግኘት ልምዶችን፣

የአእምሮ ዝግጁነትን እና ልብን ለማግኘት በብዙ ፈለግን፤ አሳዛኙ ነገር ግን የፈለግነውን አለማግኘታችን ነው።።

3ኛ. የትኛውም ዓይነት ከእናንተ ጋር የኖረውን የክርስቲያናዊ ኑሮ የተሳሳተ አስተሳሰብ ከውስጣችሁ አውጥቼ ብጥል ብዬም እመኛለሁ።። እንዲህ ማድረጉ አስደሳች እና ተመራጭ ነገር አይደለም፤ ሆኖም በእናንተ ምርጫ ግን ሊሆን ይችላል።።

1. ዋና መክፈቻ ቁልፉ ማንም የለውም

የክርስትና ኑሮን ለመኖር ማንም ቢሆን ዋና መክፈቻ ቁልፉ የለውም። በልቤ ያለው አስተምህሮ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የሚመስል ነው፤ ለብዙ ዓመታት ሕይወቱን በአረንቋ ውስጥ ያገኘ ክርስቲያን እንዲህ ነው፡- የጉዞ መርከቡ የጉዞ ምልክቷን ባንዲራ መንገድ እንደገባች ሁሉ ብታውለበልብም፣ እርሱ ግን ወደየትም አልተነቃነቀም። በዚያ የተነሳም እርሱን ስለያዘው መንፈስ ያለው እውቀት የወረደ ነው። የመርከቧ ሸራ የተወጠረች ቢሆንም፣ መርከቧ ሸንቁር ወይም አንዳች እክል እንዳለባት ሁሉ ንቅናቄ አታሳይም። በዚህ ክርስቲያን ዙሪያ ያሉ ሰዎች ሁሉ ንቅናቄ እና መሻሻል ቢያሳዩም እርሱ ግን እዚያው ያለበት ሥፍራ አረንቋ ውስጥ እንደገባ ሆኖ ያለንቅናቄ ይታያል። ይህ ሰው በዘመኑ ሁሉ እርሱን ስለያዘው የመንፈስ ቅዱስ ንፋስ ያለው እውቀት ውሱን ሳይሆን አልቀረም። የመርከቧ ሸራ የተወጠረ ቢሆንም፣ ከነበዙ ሸንቁሩ ዘላለም የሚዘልቅ ይመስላል። በእዚህ ሰው ዙሪያ ያሉ ሁሉ እድገት እና ለውጥ ሲያሳዩ፣ እርሱ ግን ከርሞ ጥጃ ሆኖ ይታያል።

አንድ ቀን ግን በአንድ ኮንፈርንስ ላይ፣ ወይም ደግሞ መጽሐፍ እያነበበ፣ ወይም በግል የጥሞና ጊዜው ወቅት፣ ነገሩን ሁሉ የሚለውጠውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አገኘ፤ ለምሳሌ የክርስቲያን እና የክርስቶስ ግንኙነት ልክ የወይን ቅርንጫፍ ከግንዱ ጋር እንዳለው ዓይነት ግንኙነት የመሆኑን እውነት አነበበ፡፡ ይህም በአንድ ምሽት ሕይወቱን አቀጣጠለው፤ ፍጹም አዲስ የሆነ መንፈሳዊ ጉልበትን ወደሚያገኝበት መንኩራኩር ውስጥም ከተተው፡፡ በመርከቡ ሸራ ላይ ያሉ ሸንቁሮችም ተጠገኑ - ታደሱ! ይህም ልክ ከእግዚአብሔር የተላከ አንዳች ንፋስ ሸራውን ወጥሮት በሙላት እና በጸጥታ እንድትሄድ እንዳደረጋት ሆነ፡፡ በውጤቱም ባለፉት ስድስት ዓመታት ባልሆነው መልኩ፣ በስድስት ወራት ውስጥ ተጨባጭ እና እውነተኛ ለውጥ አሳየ፡፡

ይህ ከሆነ በኋላም ለሌሎች እንዲህ ሲል መናገር ጀመረ፡- የክርስትናን ሕይወት በእውነት ለመኖር ዋናውና ቁልፉ ጉዳይ ዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 15ን በጥልቀት መረዳት ነው፡፡ ሌሎችም ክርስቲያኖች ከክርስቶስ ጋር ሊኖራቸው የሚገባው ጎብረት የወይን ቅርንጫፎች ከግንዱ ጋር እንዳላቸው ዓይነት ጎብረት የመሆኑን ነገር ምነው ቢረዱት፣ በእውነትም

ፍጹም አዲስ ወደሆነ መንፈሳዊ መንኩራኩር ውስጥ በመግባት እነርሱም መንፈሳዊ መነቃቃት እና ኃይል ይለብሳሉ፡፡

ወይም ደግሞ፣ ያለማቋረጥ በኃጢአት የሚጠቃን እና በውስጣዊ ወቀሳ ሳቢያ ያለማቋረጥ አንገቱን ደፍቶ በጥፋተኝነት ስሜት ሳቢያ በውስጣዊ ሽባነት የሚወጣ የሚገባውን ሰው አስቡ፡፡ እርሱ በሕይወት አረንቋ - ጭቃ ውስጥ እንደሚንቦራጨቅ ብዙ ሰው አያውቅም፡፡ ጎማዎቹ የሕይወቱ አሽከርካሪ ጎማዎች በአረንቋ-ጭቃ ውስጥ ስለሆኑም፣ የማሽከርከሪያውን ጥርስ ቢቀይር ወይ ደግሞ ጎማ ማፍጠኛውን ወደታች ቢገፋው፣ የጎማዎቹን አቅጣጫ ቢቀይርም፣ ወይም ደግሞ ነዳጅ ቢጨምርም ወይም ያለ የሌለ ሃይሉን ቢጠቀምም፣ ለውጥ የለውም፤ ከአረንቋ የሚጠያወጣው የለም፡፡

ይሁንና አንድ ቀን፣ በአንድ ኮንፈረንስ ላይ፣ ወይም መጽሐፍ ሲያነብ፣ ወይም በግል የጥሞና ጊዜው፣ ሮሜ ምዕራፍ 6ን አነበበ፡፡ ከፍሉ እንዲህ ዓይነት ሃሳብ ይዟል፡- ማንም በክርስቶስ ኢየሱስ ቢሆን አሮጌው ማንነት ይሞታል፤ አሮጌውም ኑሮ ከነግሳንግሱ በክርስቶስ ኢየሱስ መቃብር ውስጥ ይቀበራል፡፡ ስለዚህ እንዲህ ያለው ሰው በክርስቶስ ኢየሱስ አዲስ ነው፡፡

እንዲህ እንዲቆጥር እና እንዲያስብ የተጠራው ይህ ሰው፣ ልክ ከሙታን እንደተነሳ ሰው ሆኖ ሊኖር ይገባዋል። ይህ ሰው “ኃጢአት አይገዛችሁምና፤” የሚለውን ያነብባል። ስለዚህ ከዚህ ጊዜ በኋላ በሕግ እስራት - በኩነኔ እና በጥፋተኝነት ስሜት እንዲሁም ከእነዚህ ጋር ተያያዥ በሆኑ አመንምኔ - ሸባ አድራጊ የኃይል ክበብ ውስጥ አይደለም፤ እርሱ ከዚህ በኋላ በጸጋ አስደናቂ የለውጥ ምህዋር ውስጥ ገብቷል። እና ምን ሆነ? እምነት ከሮሜ ምዕራፍ 6 አስተምህሮ ጋር በተስማማ ጊዜ፣ የዚህ ሰው የሕይወት አሸከርካሪ ጎማዎች በቅጽበት ከአረንቋው ጭቃ ወጡ። ግራ ተጋብቶ፣ ተጨናንቆ የነበረው አሸከርካሪ በድንገት ራሱን ከጭቃ ወጥቶ በተደለደለ አስፋልት ላይ አገኘው፤ የአሸከርካሪውን ፍጥነት መዘወሪያ ሲጫነውም፣ የሕይወት ጎማው ለመፍጠን ሁኔታዎች ምቹ ሆኑለት - ወደፊት በፍጥነት መዘወር ጀመረ። በዚህ የተነሳም ላገኘው ሁሉ እንዲህ ይል ጀመር፤ “በክርስትና ሕይወት ቁልፉ ጉዳይ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? በሮሜ ምዕራፍ 6 ላይ እኔ ራሴን እንዳገኘሁት ራስን ማግኘት ነው።

ዋና መክፈቻ ቁልፍ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? ይህ ቁልፍ የማንኛውም በር መክፈቻም ነው፡፡ የክርስትና ሕይወት እና ኑሮ ግን ዋና መክፈቻ ቁልፍ የለውም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በየትኛውም ሥፍራ ይህ ቁልፍ እዚህ ነው ብሎ አይነግረንም፡፡ ከዚያ ይልቅ መጽሐፍ ቅዱስ በእያንዳንዱ ክፍሉ የሚያቀርብልን ነገር ቢኖር የአንድን ቁልፍ መያዣ - ማንጠልጠያ ቀለበት ነው፡፡ ጌታ እንዲህ ብሏል፡- “...ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል...” (ማቴ. 4፡4 እና ዘዳ. 8፡3)፡፡ ምሉዕ ክርስቲያን መሆን የምትፈልጉ ከሆነ፣ ምሉዑ የእግዚአብሔር ቃል ያስፈልጋችኋል፤ ምሉዕ የሚያደርገው ከእግዚአብሔር ቃል ተለይቶ አንዱ አይደለም፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስም ይህንኑ ነጥብ ነው የሚያሰምርበት፡- “የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።” (2ጢሞ. 3፡16-17)፡፡ ወንድንም ሆነ ሴት በክርስትና ሕይወት ምሉዕ የሚያደርገው ምሉዑ የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ሁሉ “የእግዚአብሔር እስትንፋስ” ነው፤ ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል ሁሉ

ለትምህርት፣ ለተግሳጽ፣ ልብን ለማቅናት፣ በጽድቅ ላለው ምክር እና የእግዚአብሔርን ሰው ፍጹም ለማድረግ ይጠቅማል፡፡ ፍጹም - ምሉዕ ክርስቲያን ለመሆን ምሉው የእግዚአብሔር ቃል ያስፈልገናል፡፡

በመዝሙር ምዕራፍ ፣ ላይ የተባረከ ሰው እንዴት ሆኖ እንደተገለጸ እስቲ እናሰላስል፡- ምስጉን - ብሩክ ነው.... “በክፉዎች ምክር ያልሄደ” (አሉታዊ ነው - ያለመሄድ)፡፡ መባረክ ትፈልጋላችሁ? ለሰዓታት “በቴቪዥን” ሥር እያሳለፋችሁ አትባረኩም፡፡ የቴሌቪዥናችሁ የበዛው ምክር በግልጽም ሆነ በሥውር እግዚአብሔርን መምሰል አይደለም፡፡ ባልተመረጠ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ሥር ሰዓታትን የሚያጠፋ ሰው በጸጋ ባለው እድገት ምንም ዓይነት ለውጥ ሲያመጣ አይታይም፡፡

“እግዚአብሔር የሌለበት” - የጎደፈ የክፉዎች ምክር የሚመጣው እውቅና ከተሰጣችኋቸው ጋዜጦች - ከወሬዎቹ ቋቶች ነው! በእነዚህ በኩል አእምሮና ልባችሁን የጎደፈ - ክፉ ወሬ እየመገባችሁ በጸጋ ማደግ አትችሉም፡፡

“ምስጉን (ብሩክ) ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ፥ በኃጢአተኞችም መንገድ ያልቆመ፥…” ፍጹም ሥርዓት አልባ የሆነውን ታዋቂ የሮክ ዘፋኝ የሕይወት ዘይቤ እያደነቃችሁ፤ በአደንዛዥ ዕጽ ተዘፍቀው ሥርዓት አልበኝነት እና በልቅ ወሲብ አነሳሽነት የተጠመቁ ግጥሞችን ለአእምሮአችሁ እየመገባችሁ፣ በጸጋ እያደጋችሁ ስለመሆኑ ልትነግሩኝ አትችሉም፡፡ “በክፉዎች ምክር” እየሄዳችሁ በጸጋ አታድጉም፤ ልታድጉም አትችሉም፡፡

“ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ፥ በኃጢአተኞችም መንገድ ያልቆመ፥ በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ። ነገር ግን . . . ደስ ይለዋል፡፡ በምን ደስ ይለዋል? ለክርስትና ሕይወት ታላቁ የመከፈቻ ቁልፍ ነው የሚለው? ቃሉ እንደርሱ አይደለም የሚለው! ቃሉ የሚለው እንደዚህ ነው፡- የተባረከ - የምስጉን ሰው ደስታው “በእግዚአብሔር ሕግ” ነው፤ ይህም የተገለጠ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፡፡ ይህ ሰው የእግዚአብሔርን ቃል ቀን እና ለሌት ያስባል፡፡ “እርሱም በውኃ ፈሳሾች ዳር እንደ ተተከለች፥ ፍሬዋን በየጊዜዋ እንደምትሰጥ፥ ቅጠልዋም እንደማይረግፍ ዛፍ ይሆናል፤ የሚሠራውም ሁሉ ይከናወንለታል።”

ለክርስትና ሕይወት እንደ መክፈቻ ዋና ቁልፍ የሚታይ አንድም ነገር የለም፡፡ አለው የሚለው አስተሳሰብ የእግዚአብሔርን ቃል አጠቃላይ መዋቅር፣ በተለይ ደግሞ የአዲስ ኪዳንን መልዕክቶች የሚያፋልስ ነው፡፡

የአዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች ምን ዓይነት ችግር ነበረባቸው? የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን የነበረባትን ችግር እንደ አንድ ምሳሌ እንውሰድ፤ እርስ በእርስ የመከፋፈል ችግር ነበረባቸው፤ የግብረገብየለሽነት ችግርም ነበረባቸው፤ የጋብቻ እና የክርስትና ነጻነት የት ድረስ ነው? የሚለውም ጥያቄ ነበራቸው፤ ይህን ማድረግ አለበኝ ይሆን? ወይስ ያን ማድረግ ይገባኝ ይሆን? እዚህ መሄድ አለብኝ ይሆን? እዚያ መሄድ የለብኝም ይሆን? ይሉ ነበር፡፡ ራስን ስለመካድ እና ስለመንፈሳዊ ስጦታዎችም ያልተመለሱ ጥያቄዎች ነበሯቸው፡፡ የክርስትና ሕይወት መክፈቻ አንድ ዋና ቁልፍ ቢኖረው ኖሮ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ ለእነዚህ ሰዎች አይሰጣቸውም እና እንዲህ አይላቸውም ነበር፡- “ይሽውላችሁ ቁልፉ፤ ችግራችሁ ምንም ቢሆን፣ የችግራችሁ መክፈቻ ቁልፉ ይህ ነው፤…” እርሱ ግን እንዲህ አላላቸውም፡፡

ለክርስትና ሕይወት መከፈቻ ቁልፉ አንድ ነው የሚለውን ትምህርት መቃወም አለባችሁ፡፡ የእኛ ሥጋዊ ማንነት እንደሚፈልገው ዓይነት ለክርስትና ሕይወት መክፈቻ የሚሆን አንድ ዋና ቁልፍ የለም!

2. ከውጥረት ማምለጫ መንገድ የለም

በክርስትና ሕይወት ከውጥረት እና ከግጭት ማምለጥ አይቻልም። ይህን ስል ግን የክርስትና ሕይወት ሁሉ በግጭት እና በውጥረት የተሞላ ነው ማለቴ ግን አይደለም። እርስ በእርሱ የተምታታ እንደሆነ ልገልጸው የምፈልገው አስተምህሮ ግን ይህ ነው፡- በአንድ ኮንፈረንስ ላይ ሰባኪው የጠቀሰውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ከአውዱ ውጪ አድርጎ ከ“ሺቦሌት” ጋር አቆራኝቶ ወይም ከዚህ ቃል አውጥቶ፣ ወይም ደግሞ “የክርስቶስን ሕይወት ማዳን”፣ ወይም “የመጠጊያን ሕይወት” እያብራራ ይናገራል። ሰባኪው የክርስትናን ሕይወት በተመለከተ የእርሱን ምልከታ እና እሳቤ ካብራራ በኋላ፣ እንዲህ የሚል ጥያቄ አቀረበ፡- “ከኃጢአት ጋር ባለው የውስጥ ትግላችሁ ሳቢያ ሰልችትችሁ እና ደክማችሁ - ታክታችሁ ይሆን? በጸሎት መጋደሉስ አድክሟችሁ ይሆን? በነደፈ ሃሳባችሁ ሳቢያ ከራሳችሁ ክፋት፣ ኩራት እና ቅናት ጋር መታገሉ አንገፍግፏችሁ ይሆን? እንዲህ ባለው የማያቋረጥ እና ደባሪ ግጭት ምክንያት ተሰላችታችኋል?

ምላሹስ ምን ይሆን? ማንኛውም እውነተኛ ክርስቲያን እዚህ ጋር ቆሞ፣ እንዲህ ሲል ወደ እግዚአብሔር ይጮኻል፡- “አ እግዚአብሔር ሆይ፣ ድካሜን ተመልከት፤ አንድ ቀን፣ አዎ ጌታ ሆይ ከልቤ እና ፍዘትና ድካም የምወጣበትን አንዲትን ቀን ለማየት ሁሉን እከፍላለሁ፤ አዎ፣ የአእምሮን ስብራት፣ ከውስጥ እና ከውጪ በሆነው የኃጢአት መሳብን ለመላቀቅ… ካለ በኋላ፣ ከዚያም ሰባኪው እንዲህ አለ፡- “በውጥረት ምክንያት ከደከማችሁ፣ በግጭት ምክንያት ከሰለቻችሁ፣ የተወሰኑ ርምጃዎችን ከተራመዳችሁ፣ ክርስቶስ ሕይወቱን በእናንተ ውስጥ እንዲሠራ በማድረግ ከውጥረት እና ከግጭት ነጻ ያደርጋችኋል። ከዚያም በመንፈስ ቅዱስ ትሞላላችሁ፤ በመንፈስ ቅዱስም ትወሰዳላችሁ፤ ከዚያም እነዚያ ውጥረት እና ግጭቶች ከነመነሻዎቹ እና ከነዓላማዎቹ ታሪክ ይሆናሉ፤ እናንተ እግዚአብሔርን በመጠጊያነት በመረጣችሁ ጊዜ ሁሉ የኋላ ታሪክ ብቻ ይሆናሉ። ግጭት እና ውጥረት በተከሰተባችሁ ቅጽበት፣ አንድ ነገር አስተውሉ፤ እግዚአብሔርን መጠጊያ ካደረጋችሁበት ሕይወት ወጥታችሁ ወደ አሮጌው ልምምዳችሁ ተመልሳችኋል ማለት ነው። ልብ አድርጉ ይህ አስቂኝ ስዕል አይደለም። ይህ በአንድ መጽሐፍ ውስጥ ገጾችን ሁሉ በከፈታችሁ ቁጥር የምታነቡት ነገር ነው። እንዲህ ካሉት መጻሕፍት

ተጠንቀቁ! ከልባችሁ ከተቀበላችኋቸው፣ ሃሳባቸው እውነተኛ ወዳልሆነ ዓለም ወይም ወደ ተጠራጣሪነት ይከቷችኋል።

ከእግዚአብሔር ቃል ከራሱ፣ ስለቃሉ ምን ዓይነት የተስማማ ማረጋገጫ ማቅረብ እችላለሁ?

(1) የጎደፈ እና ኃይል የተሞላው ኃጢአት ከድርጊቶች ጋር በእኛ ውስጥ መመሸጉ እውነታ፤ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ የሚለውን አስቡ፡- “ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና፥እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ፤ ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም።” (ገላ. 5፡17)። ጳውሎስ ከግጭት እና ከውጥረት ፈጽሞ፣ ሙሉ በሙሉ ነጻ ትሆናላችሁ የሚል ነገር አልተናገረም። እርሱ የሚለው በሥጋ ተጽዕኖ ውስጥ መውደቅ የለብንም ነው። በየትም ሥፍራ ሥጋ የሥጋን ሥራ ይቃወማል አይልም፤ ሥጋ የመንፈስን ሥራ ሲቃወም፣ ያኔ ግጭት ይፈጠራል።

በጊዜ ሂደት የተመሰከረ - የተረጋገጠውን የሮሜ 7፡14 -25ን ትርጓሜ ይጎለሁ፤ ይህም የአዲሱ ሰው የየዕለቱ አሰቃቂ ግጭት ገለጻ ነው።

“መልካም ሳደርግ”፣ በግልጽ እንደሚታየው መልካም በማደርግበት ሁኔታ ውስጥ ማለት ነው፤ “በውስጤ ሌላ ሕግ አገኛለሁ።።” መንፈሳዊውን ሃሳብ ባማሰላሰላችሁ እና ባደረጋችሁ ልክ፣ ተቃዋሚው የኃጢአት ድርጊት በኃይለኝነት እና በተገዳዳሪነት ይገለጣል።። ሥራ-ብዙ ሆናችሁ በዋላችሁበት በዚህ ቀን መጨረሻም ቤታችሁ ስትመጡ እንዲህ ትላላችሁ፡- “እስቲ ቴሌቪዥኔን ከፍቼ ዜናዎችን ልመልከት!” ይህንን ሃሳብ ስታቀርቡ ታዲያ በሥጋችሁ የመሸገው ኃጢአት በድንገት ኃይል ሲላበስ ተሰምቷችሁ አያውቅም? … ደግሞ ሥራ-ብዙ ሆናችሁ በዋላችሁበት ቀን መጨረሻ እቤት እንደገባችሁ፣ ለራሳችሁ እንዲህ በሉት “በዚህ ማለዳ ከቃሉ ጋር የነበረኝ ጊዜ በጣም ጥቂት ነበረች፤ ስለዚህ በጥሞና ለሠላሳ ደቂቃ ቃሉን ማንበብ ይኖርብኛል።።” … ከዚያ ምን ይሆናል? በቅጽበት ድካም ድካም ይላችኋል፤ ከዚያም እንዲህ ትላላችሁ፡- “ሳይታወቀኝ ለካ እንዲህ ደክሞኛል!” ድባቴ ልብ እና አእምሮአችሁን ይከብበዋል።። ከዚያም በጥቅሉ መንፈሳዊነት ይርቃችኋል - ሽባነት ይሰማችኋል።። በዚህ ሳቢያም በዚህ ሁኔታ የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ እግዚአብሔርን እንዳለማከበር ሆኖ ይሰማችኋል።። የዚህ መነሻው - ምክንያቱ ግን ምንድነው? በሥጋችሁ ውስጥ የመሸገው ኃጢአት ነው።።

ከጓደኞቻችሁ አንዱን ለማናገር ስልክ ስታነሱ፣ ድካም ይሰማችኋል፤ ነገር ግን ለአምስት ደቂቃ ከተነጋገራችሁ በኋላ ግን አእምሮአችሁ ፈጣን ምላሳችሁም የሰላ ይሆናል! እስቲ አምስት ደቂቃ በጸሎት ለማሳለፍ ወስኑ፤ ያኔ ምን የሚሆን ይመስላችኋል? አእምሮአችሁ ድንዝዝ ይልና ሃሳባችሁ ብትንትን ይልባችኋል፤ ምላሳችሁም ልክ በሥጋ ቤት ከዚያ እና ከዚህ በሜንጦ እንደተወጠረ ሥጋ እስርስር ይላል።

እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ በሥጋችሁ የመሸገው ሥጋ የዚህን ምድር ኑሮ ጨርሳችሁ ወደ ሰማያዊው ቤታችሁ እስክትሄዱ ድረስ በእናንተ የማይደሰት የመንገድ አጋራችሁ ሆኖ ይዘልቃል። የክርስትና ሕይወትም ከውጥረት እና ከግጭት ነጻ ሊሆን የማይችለውም ለዚያ ነው።

(2) ዓለምም ደግሞ በእረፍት-አልባነት፣ በኃይል የክፋት ተጽዕኖዋን እና ግፊቷን ታሳድርብናለች። ሐዋርያው ጳውሎስ እንደሚነግረንም፡- “በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።” (ሮሜ. 12፡2) ጂ.ቢ. ፊሊፕስ የዚህን ክፍል ሃሳብ በሚከተለው መንገድ በትክክል

አስቀምጦታል፡- “ዓለም በፈለገችው መንገድ ጨምቃ፣ አድፈጥፍጣና ጠፍጥፋ እንድትጋግራችሁ - እንድትቀርጻችሁ አትፍቀዱ::” የዚህ ዓለም ሥርዓት የተቀናጀ (ግን እግዚአብሔርን ከቅጥር ውጪ ያደረገ) ሕልው ነው:: በአደረጃጀቷ፣ በግቧ፣ በሃሳቧ፣ በአስተሳሰቧ አቀራረጽ እና በፍልስፍናዋ ለእግዚአብሔር ቃልና ሕግ ጠላት ነች:: “ዓለም” በእግዚአብሔር አንጻር የቆሙ ዳግም ያልተወለዱ - የፍጥረታዊ ሰዎች የተሞላችም ነች::

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን፣ ዓለም ለእርሷ የኑሮ ሥርዓት ጀርባቸውን ሰጥተው ከካዷት ጋር ዳግም ወደ ሥርዓቷ ያለማስገባት ውል አትፈጽምም:: ስለዚህ በኃይል ያለማቋረጥ የመጭመቅ፣ የማድፈጥፈጥ እና የመጠፍጠፍ ደግማም የመቅረጽ ሙከራ ታደርጋለች፤ ቢሳካለት ወደ እርሷ አምላክ-የለሽ ሥርዓት ለመመለስም ትጥራለች:: በሁሉ ዓለማውያ ተቀባይነት ባለው የሥርዓቷ ቀኖና በተቃራኒ ሆኖ አንድ ሰው ካሰበ እና ካደረገ እብደት የተሞላው ቁጣዋ ይነዳል:: የእርሷ የኑሮ ቀኖና የሚታየውን ማመን ነው፤ ለሚጨበጠው ነገር ዋጋ መስጠት ነው፤ የሚታመነው በሰውነት - በእጅ ላይ ያለው፣ በባንክ ደብተር ላይ ያለው፣ በቤት እና

በመሬት ያለው ቁሳዊ ነገር ነው፡፡ እግዚአብሔር የሚለው ግን ከዚህ በተቃራኒ ዋጋ ያለው በሰማይ ያለው መዝገብ - ሃብት ነው፡፡ ዋጋ ያለው የተደበቀው የልብ ውበት ነው፤ ስለዚህም ነገር ይህች ዓለም አንዳች አታውቅም፡፡

ዓለም እንደተለማመደችው - እና ሁልጊም እንደምትለማመደው በአማኝ ላይ እረፍት-የለሽ ተጽዕኖአዊ ግፊቷን ማድረጓ፣ በአማኙ ላይ ውጥረትን እና ግጭትን ከማድረግ ጋር የተቆራኘ ነው፡፡ ሐዋርያው ዮሐንስም እንዲህ ብሎ መጻፉ ለዚያ ነው፡- *“ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለ ሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ፥ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም።ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘላለም ይኖራል።”* (1ኛ ዮሐ. 2-15-17)

ለእኔ አስፈሪ ከሚሆኑብኝ ነገሮች አንዱ (ይህን ለማየት በእድሜ መነልበቴን በማስታወስ) ይህ ነው፡- በወጣት ወንዶች እና ሴቶች ፊት ላይ

ያለውን ነገር አነብና፣ አሁን ለእግዚአብሔር ነገር የጋለ ፍላጎት እና ስሜት እንዲሁም የሚያድስ ነገር ያላቸው ልጆች፣ ከዐሥር ዓመታት በኋላ ይህንኑ የጋለ ነገራቸውን ይዘው ይዘልቁ ይሆን ስል ራሴን እጠይቃለሁ፡፡ ከምድረገጽ እንደጠፋው እንደሞሪሽየሱ የመሬት ወፍ ይጠፋሉ፤ ለመንፈሳዊ ነገር ሙት ይሆናሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ምን ይሆናል? ኢየሱስ እንዳለው፣ አንዳንዶች ቃሉን ወዲያውኑ እንደ መልካም መሬት በደስታ ይቀበላሉ፤ ነገር ግን አረም ባደገ ጊዜ ቃሉን አንቆ እንደ መልካም ተክል እንዳያድግ ያደርገዋል፡፡ ኢየሱስ አረሙን በምን መግለጫ እንደተጠቀመ ታውቃላችሁ? የዚህ ዓለም ፍቅር እና የዚህ ዓለም ሃሳብ ናቸው፡፡ አካሄዳችሁ ከዓለም የተለየና ከንቱነቷን የሚገልጥ ከሆነ፣ ዓለም ትጠላችኋለች፡፡ የዚህችን ዓለም ነገሮች አላልታችሁ ይዛችሁ፣ የምትኖሩት ለራሳችሁ እና ለግዛተ-እኔ ካልሆነ፣ ፍቅራችሁ እና ጠንካራ ፍላጎታችሁ - ሕይወታችሁም በኢየሱስ ክርስቶስ ቁጥጥር ሥር ከሆነ እና ለመንግሥቱ ጉዳይ ነፍሳችሁን የምታፈስሱ ከሆነ፣ በመጨረሻ በሰማይ መዝገብ የከበረ ሃብት ይኖራችኋል፤ ግን ደግሞ እናንተ ለዓለም የማይቋረጥ የቁጣ ምክንያት ትሆናላችሁ፤ ዓለምም እናንተን ልክ እንደክፉዎቹ ሰዎች ካላጎደፈች እና ካላከፋች አታርፍም፡፡ ሆኖም ራሳችሁን “ክቡር” ለማድረግ

“በቂ ሃይማኖት” አለኝ የምትሉ ከሆነ ግን፣ ዓለም ትወዳችኋለች፤ ለምን ብትሉ፣ እንዲህ ያለውን ሁኔታ የእርሷ ፍልስፍና አይቃወመውም፤ እንዲያውም እንዲህ ያለው አስተሳሰብ ያለው ሰው በዓለም ሃውልት የሚቆምለት ዓይነት ይሆናል።

ከግጭት እና ከውጥረት ማምለጫ መንገድ የለም። ነገር ግን ዓመታት ባለፉ እና እግዚአብሔርን የመምሰል ልማድ ሥፍራ እየተቆጣጠረ በሄደ ቁጥር፣ ችግሮች ቀለል እያሉ አይመጡ ይሆን? እዚህ ምድር ላይ ግማሽ ምዕተ-ዓመት እንደኖረ እና ከእነዚህ ዓመታት ውስጥ 32ቱን በክርስትና ሕይወት እንደኖረ ሆኜ ስመለከተው፣ የፍልሚያው መጠን እየከፋ ሲመጣ ያየሁት ክርስትናን ከጀመርኩበት ጊዜ ይልቅ አልፌ ወደወደያኛው ጎዳና ለመሻገር በቀረብኩበት ጊዜ ነው ማለት እችላለሁ። ጆን ቡንያን ይህን ጉዳይ በትክክል አስቀምጦታል፤ አማኞች ይህችን ዓለም ተሰናብተው ወደዚያኛው ዓለም እስኪሻገሩ ጊዜ ድረስ እረፍት አይኖርም።

(3) ዲያቢሎስ አድኖ ስለማነቅ እና ስለመዋጥ ያለውን ክፉ ናፍቆቱን በማስታወስ ረገድ ብዙ የሚያስታውሰን ነገር አለው። ጴጥሮስ አበክሮ

ያሳሰበውን አትርሱ፤ “በመጠን ኑሩ ንቁም፥ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና፤” … ዲያቢሎስ የሚዞረው ሰዎችን ለማስደነቅ ከእንስሳት መጠበቂያ እንደወጣ እና ተንኮል እንደሌለበት እንስሳ ነው እንዴ? አይደለም፤ በዙሪያችን የሚዞረው ለሥራ ነው! እርሱም ትኩረታችንን ወደ እርሱ እንድናደርግ ነው፡፡ እርሱ በዙሪያችን ሲሽከረከርም ምን ፈልጎ ይሆን…? በአጭሩ ወደእርሱ የሚመጣውን በመርዛማ ጥርሶቹ ነድፎ የጥርሱን አሻራ ለመተው ነው፤ ብዙ ሳይሆን ትንሽ ንክሻ ይበቃዋል! የሚፈልገው በኃይል እና በጭካኔ የሚነጥቀውን ነው፡፡ ለዚህም ነው ሐዋርያው ያዕቆብ “ዲያብሎስን ተቃወሙት፤ ከእናንተም ይሸሻል” ሲል ያሳሰበው (ያዕ. 4፡8)፡፡ እንዲህ ያለውን ማሳሰቢያ በሐዋርያው ጳውሎስም ምልዕክት ላይ እናገኛለን፡- *“መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፤ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ሰፍራ ካለ ከክፉት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ፡፡”* ጳውሎስ በመልዕክቱ የከበረውን የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት እስኪታገኙ ድረስ ነው እንጂ፣ ከዚያ በኋላ ጦርነቱ ይቆማል አይልም፤ ወይም ደግሞ ወደ ሆነ መንፈሳዊ ጉባኤ ሄዳችሁ ስለመሸሸግ ሕይወት አንዳች ምስጢር እስክትማሩና እስክታውቁ

እንጂ ከዚያ በኋላ ፍልሚያው ያበቃል አላለም! እንደርሱ አላስተማረም! ከእውነታው ጋር የሚኖር እውነተኛ ክርስቲያኖች ከሆናችሁ፣ ዲያቢሎስ የሚውጠውን በጉጉት እንደሚናፍቅ አውሬ በጭካኔ ሊያደባያችሁ እና ሊውጣችሁ ነው በዙሪያችሁ ይሸከረከራል።

(4) በተስፋ ድነናል። የዳንነውም ወደፊት ባለው ዘላለም ውስጥ እናርፋለን በሚል የተስፋ ዐውድ ነው። አሁን ያለን ሁሉ እንደቀብድ የተቀበልነው ነው። ይህ እንዴት እንደሚሠራም አስታውሱ። በእናንተ ያለው የእግዚአብሔር ሥራ ሲያልቅ፣ እናንተ ምን የምትመስሉ ይመስላችኋል? መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው ክርስቶስ ኢየሱስን ትመስላላችሁ። በእርሱ የከበረ ገጽታ የተሠራው የሰውነት ቁመና ይኖራችኋል (ፊል. 3፡21)። የእርሱን መንፈስ ገጽታ ትለብሳላችሁ። እግዚአብሔርን አትሆኑም፤ ነገር ግን፣ የኃጢአት ዘር እና ግሳንግሱ ሁሉ ከእናንተ ይወገዳል፤ በዚህ ሳቢያም የፍጥረትነት ልካችሁን ጠብቃችሁ ፍጹም የማፍቀር ብቃትን ትገናጸፋላችሁ። እስቲ አስቡት! በዚህ ሁኔታ ለአንድ ቀን አይደለም፤ ነገር ግን ለዘመን ዘመናት ያለ አደናቃፊ ሃሳብ፣ ያለጎደፈ ሃሳብ እና ያለ ክፉ ቅናት ትሆናላችሁ።

እግዚአብሔር የለየን ለዚህ ዓይነቱ ፍጽምና ነው፡፡ ያኔ የኃጢአት ነቁጥ የሌለበት አእምሮ እና መንፈስ ይኖረናል፤ ፍጹም ቅዱስ የሆነ ሃሳብ የሚያፈልቀውን የልብ የሚሸከም ሰውነት ይኖረናል፡፡ እንዲህ ያለውን ልምምድ በተለይ ጌታ ለእኛ ቅርብ እና ውድ እንደሆነ በተሰማን ጊዜ ተረድተናዋል፤ እንዲህ ባለው ጊዜ ከዚህ “ለሞት ከተሰጠ ሰውነት” ነጻ ወጥተን እንደመላዕክት ማገልገልን ናፍቀን እናውቃለን፡፡ ይህም ከእግዚአብሔር ጋር ያልተቋረጠ ጎበረት እንዲኖረን ከመፈለግ ንጹህ ደስታ በመነጨ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ጊዜ ሲሄድ ያ ድካም ተመልሶ ሰውነታችሁን ይከበዋል፤ ከዚያም ተስፋ መቁረጥ እና ድባቴ ይወራችኋል፡፡ እውነታው ግን ይህ ነው፤ እኛ በሰውነታችን እና በመንፈሳችን ለፍጹምነት ተመርጠን ምልክት ተደርጎብናል፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ፍጹምነትን አሁን በምድር ላይ እንዲሆን አላደረገም፤ አላጸደቀም፡፡

ውጤቱ ምንድነው? ውጥረት! ምክንያቱም በተስፋ ድነናል፤ ተስፋው ደግሞ ገና አልተጨበጠም፤ ውጥረት አለ፤ ግጭት አለ፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ከጉዞዎቹ በአንዱ ባረፈበት ወይም በተቀመጠበት ቤት መሆን

ምን ማለት እንደሆነ እስቲ እናስበው፡፡ እርሱ እየጸለየ ባለበት ሁኔታ ወደ ክፍሉ መሄድ ችለን ቢሆን እና የሐዋያውን የጸሎት ድምጽ ሰምተነው ቢሆን ድንቅ ነገር አልነበረም ወይ? ነው፤ ነገር ግን፣ አንዳንድ ጊዜ ግን ምን ዓይነት ድምጽ ሊሆን እንደሚችል ታውቃላችሁ? የማቃሰት - የመቃተት ድምጽ ልትሰሙ ትችላላችሁ! ይህን በሰማችሁ ጊዜም፣ ለራሳችሁ፣ ይሄ የሐዋርያው ጳውሎስ ክፍል ሊሆን አይችልም፤ ሌላ ክፍል ብፈልገው ይሻላል!” ልትሉም ትችላላችሁ፡፡ ክፍሉ ግን የጳውሎስ ነው፡፡ እርሱም እንዲህ ሲል ይመልሳል፡- “በድንኳን ያለን እኛ ከብዶን እንቃትታለን” (2ኛ ቆሮ. 5፡4)፡፡ ጳውሎስ ያቃሰተባቸው - የቃተተባቸው ጊዜዎች አሉ፤ ምክንያቱም በዚያ በጸጋ በተለወጠው ቅዱስ ልቡ ውስጥ ክርስቶስን ለማገልገል የሚቃጠል - የሚንበለበል ፍቅር ነበረው፡፡ ግን ደግሞ ይህን ደካማ ሰውነትም ተሸክሞ ነበር፡፡ “ነገር ግን የውጭው ሰውነታችን ቢጠፋ እንኳ የውስጡ ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል።” በዚህም ምክንያት ቃትቷል፡፡ ሮሜ ምዕራፍ 8 የሚነግረን ተመሳሳይ ነገር ነው፡- “ፍጥረት ሁሉ እስከ አሁን ድረስ አብሮ በመቃተትና በምጥ መኖሩን እናውቃለንና። እርሱም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን የመንፈስ በኩራት ያለን ራሳችን ደግሞ የሰውነታችን ቤዛ የሆነውን ልጅነት እየተጠባበቅን ራሳችን በውስጣችን

እንቃትታለን" (ሮሜ. 8፡22-23)። ይህም ማለት ውጥረት እና ግጭቱን ነው የሚነገርን! ሆኖም ይህ የመንፈሳዊ ጉዳይ ደጋፊ አካል ሳይሆን በአጠቃላይ መንፈሳዊነት መሆኑ ይሰመርበት፡፡ እንደ አጠቃላይ ስምምነት የመቀበላችን ምልክቶች የሆኑ መዋተቶች እና ማቃሰቶች አሉ፡፡ ከውጥረት ማምለጫ መንገድ የለም፡፡ ከውጥረት እና ከግጭት ማምለጫ አዲስ መንገድ እንዳገኛችሁ የምታስቡ ከሆነ፣ ከእውነታው ውጪ ሆናችኋል፡፡

የወረሰነውን ማቀብ አንችልም

በክርስትና ሕይወታችን ድነት ያገኘንባቸውን እና የተዋጀንባቸውን የማንነት አላባቸዎች ማቀብም ሆነ መቃወም አይቻልም፡፡ የተዋጀ ሰው የማንነት ውርሶች ምንድናቸው? እጆቹ፣ ዓይኖቹ፣ ጆሮዎቹ. . . ናቸው፡፡ ደግሞም ከእውቀት ጋር የተያያዘ ውርሶችም አሉት፤ አእምሮ እና በነገሮች ላይ የሚሰጠው ውሳኔ - ፍርድ፣ ለድርጊቶች ምላሽ የሚሰጥበት ስሜታዊ ውርስ እንዲሁም የሰውነት ፈቃድን የመጠቀም ውርስ ወይም የፈቃድ ውርስ አለው፡፡ የሰውነቱን ጥያቄዎች የማስተናገድ ውርስ፤ ይህም የምግብ ፍላጎትን፣ ውስጣዊ ፍላጎትን ይህም ሥነ-ልቦናዊ እና አካላዊውን

የሚመለከት ሲሆን፣ እነዚህም አንዳቸው ከአንዳቸው ጋር የተቆራኙ ወይም የተሰናሰሉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እነዚህም የሰውነታችን ውርሶች ናቸው፡፡ እግዚአብሔር ኃጢአተኛን ዳግም ሲወልደው የሰውነት አዳዲስ ውርሶችን አልሰጠውም፤ ወይም ደግሞ ያሉትን የሰውነት ውርሶቹን መግደል እና ማጥፋት አላስፈለገውም፡፡ በዚያ ፈንታ፣ የወረሳቸውን የሰውነት አላባዎች በአስደናቂው የጸጋው አሠራሩ አዳዲስ ተግባራት እና እይታዎችን እንዲኖሯቸው ነው ያደረገው፡፡ እግዚአብሔር በዳግም ውልደት አሠራሩ የሰውነትን ውርሶች በሚያጠፋ፣ በተጻረረና በሚገድል መንገድ አልሠራም፤ አዳዲስ አላባዎችን መፍጠርም አልፈለገም፡፡ ይህም ማለት ወደክርስትና ሕይወት የተጠራነው አእምሮአችንን እና ውሳኔዎቻችንን፣ የማሰብ አቅማችንን እና ግምገማችንን፣ ፍቅራችንን እና ስሜታችንን እንዲሁም ፍላጎታችንን እና ዝንባሌአችንን ሁሉ ለእርሱ በሙላት ለማስገዛት ነው፡፡

ይህንን መርህ ሳብራራ ለማድመቅ እና ለማጉላት የፈለግኹት ምን ይመስላችኋል? ብዙ ሰባኪዎች እና አማኞች እንዲህ ብለው ያስተምራሉ፡- “ክርስትናን ለመኖር ባለው ጥረትህ እንዳይሳካ ያደረገው ችግርህ ይህ ነው፤ እግዚአብሔር ግን አንተ እንዲህ እንድትኖር ፋቃዱ አይደለም፡፡ ራስህን

ለማዳን በመስቀል ላይ ሄደህ አንተ እንድትሰቀል እንዳላደረገ ሁሉ፣ አሁንም እግዚአብሔር አንተ በራስህ ክርስትናን እንድትኖር አይጠብቅብህም፡፡ እርሱ ከአንተ የሚጠብቀው ነገር “እንድትፈቅድለት እና ኢየሱስ በአንተ ሕይወት ራሱን እንዲገልጥ ነው፡፡”

እኔ ይሄንን “የማንቆርቆሪያ ጽንሰ-ሃሳብ” እለዋለሁ! ይህም አሠራር እናንተ በአጠቃላይ እንደመጠቀሚያ እቃ ሆናችሁ የእርሱ ሕይወት እየፈሰሰ የሚወጣበት ዓይነት መሆኑን ነው የሚያሳያችሁ፡፡ እርሱ በእናንተ ሕይወት በመኖሩ ታዲያ ከሰውነት ውርሶቻችሁ የበዙት እንዳይሠሩ ማዕቀብ ይጣልባቸዋል ማለት ነው! በዚህ ጉዳይ ግራ የመጋባታችሁ ምክንያት ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ፣ አእምሮአችሁን ብቻ መጠቃማችሁ ነው፡፡ አእምሮአችሁን ብቻ መጠቀም የለባችሁም፡፡ በዚህ ነገር አእምሮአችሁ ከመሥራት ይገደብ፡፡ እና የክርስቶስ አእምሮ በእናንተ አእምሮ ውስጥ መሥራት ይጀምር፤ ፍቀዱለት፡፡ ችግሩ ግን ፈቃዳችሁን ትጠቀማላችሁ፣ የፈቃዳችሁንም ትሩፋት በመንገዳችሁ ላይ ታገኛላችሁ፡፡ አሁን እስቲ ፈቃዳችሁን ተቃረኑት፤ በዚያ ጊዜም ክርስቶስ ኢየሱስ በእናንተ አልፎ ፈቃዱን ይፈጽማል፡፡

ይህ ምናልባትም በጣም መንፈሳዊነት ሊመስል ይችላል፤ ነገር ግን ይህ ጭብጥ - አልባ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ነው፡፡ በተለይ የዚህ ዓይነቱን ትምህርት የሚያሳዩ ሦስት ገለጻዎች ላይ ማነጣጠር እፈልጋለሁ፡-

(ነኛ). ክርስቶስ ኢየሱስ በሰው ውስጥ የመኖሩ ሚዛኑን ያልጠበቀ ዶክትሪን የሃይማኖት ሕግ እና አስተምህሮ

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ክርስቶስ በእኛ ውስጥ የመኖሩ አስተምህሮ ተቀምጧል፡- “ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው” (ገላ. 2፡20)። ብዙ ቀና ሃሳብ ያላቸው ሰዎች ይህንን ሃሳብ ከተከታዮቹ የእግዚአብሔር ቃል ክፍሎች ጋር ያቋረጧቸዋል፡- “ሕይወታችሁ የሆነ ክርስቶስ...” (ቆላ. 3፡4)፤ “በሕይወቱ እንድናለን” (ሮሜ. 5፡10)፤ ይህም የክፍሉን የቀረበ አንድምታ - አውድ እና የእምነትን ምስክርነት (የመጽሐፍ ቅዱስን አጠቃላይ ምስክርነት) ችላ በማለት፣

ክርስቶስ በእኛ ውስጥ ከመኖሩ ጋር ያቆራኙታል። ስለዚህ ማለት የምንችለው ነገር ቢኖር፣ ይህ ትምህርት በሚያሳዝን ሁኔታ ሚዛን የጎደለው መሆኑን ነው። ክርስቶስ በሰው የመኖሩ አስተምህሮ እንደ ዎችማን ኒ፣ ኤ.ቢ. ሲምሰን እና ሚስ ሃና ዊዝሃል ስሚዝ ባሉት ጸሐፍት ይገለጻል። እንደ ጸሐፊዎቹ አባባል፣ ክርስቶስ በሃሳባችሁ ተቃርኖ እና ተአቅቦም እያለም እንኳ፣ ሰዋዊ ፍርዳችሁ፣ ፈቃዳችሁና ፍቅራችሁ እያለም እንኳ፣ ... እንዲህ ባለ ሁኔታችንም እንኳ ክርስቶስ በትክክል በእኛ ሕይወት ይገለጣል።

(2) ከክርስትና ሕይወት ተነጻጽሮ የወጣ - የተደመደመ ዋስትና የለሽ አመክንዮ

ከዚህ ትምህርት የተወሰኑት ከክርስትና ሕይወት ተነጻጽሮ የወጣ እና የተደመደመ ዋስትና-ቢስ አመክንዮ ነው። የክርስትና ሕይወት በአንድም ሆነ በሌላ፣ ከወይን ግንድ እና ቅርንጫፎቹ ጋር ተመሳስሎ ይኖረው ይሆን? አዎ፣ ነገር ግን በዚህ ተመሳስሎ ምን ሊሠራ እንደሚችል አስተውላችሁ ይሆን? ከሌሎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮዎች ተላቅቆ የቀረ ነው። ሥነ-መለኮቱ ሁሉ ከእዚህ የወጣ ነው።

አንድ ሰባኪ ጠየቀ በተባለው መንገድ ላስቀምጥላችሁ፤ “እየበሰለ ባለ የብርቱካን ፍሬ አጠገብ አልፋችሁ የምታውቁ ምን ያክሎቻችሁ ናቸሁ?” ከአድማጮቹ አንዳንዶቹ እጆቻቸውን እንዳነሱ፣ ተናጋሪው ሰባኪ ሌላ ጥያቄ አከለ፤ “አሁንም አንድ ነገር ልጠይቃችሁ፤ ማንጎውን ለማቅረብ ማስታወቂያ የሠራ የማንጎ ዛፍስ አይታችሁ ይሆን?” ...እያንዳንዱ የሚያማምሩ የዛፉ ቅርንጫፍ የሚያደርጉት ነገር ቢኖር ራሳቸውን ከግንዱ ጋር ማቆራኘት እና ከግንዱ የሚቀርብላቸውን ፈሳሽ ምግብ መሳብ ነው፤ ያኔ ማንጎው በራሱ ጊዜ በላያቸው ላይ ይበቅላል፤ ይገለጣል፤ ከመንፈስ የተወለደ ያማረው የመንፈስም ፍሬ ሁሉ የሚታየው በተመሳሳይ መንገድ ነው::

አንዳንዶችም ድምዳሜያቸውን ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው አመሳስሎ ጋር በማዛመድ ከኢየሱስ ሞት ጋር የመሞትን፣ የመቀበርን እና የመነሳትን አስተምህሮ ያራምዳሉ:: እንዲህ ሲሉም ይጠይቃሉ:- “ከክርስቶስ ጋር ሞተናል? እስቲ ወደ ሞተ ሰው መዓዛው እጅግ የሚያውደውን ሽቶ ይዛችሁ ሄዳችሁ አፍንጫው ጋር አድርጉለት፤ ዋው ምን ዓይነት ውብ ሽቶ

ነው! የሚል ምላሽ ይሰጣል? በፍጹም አይሰጥም! ስለዚህም በእውነት ከክርስቶስ ጋር ሞታችሁ ከሆነ፣ ኃጢአት በእናንተ ላይ ይግባኝ ሊል አይችልም።" ይህ ግን ዋስትና የሌለው እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ ድምዳሜ ነው፤ ከክርስትና ሕይወትም ጋር አብሮ የሚሄድ አይደለም!

(3) ቅድስና በእምነት ብቻ የሚል ትክክል ያልሆነ አስተምህሮ

ትምህርቱ እንዲህ ነው፤ ጥፋተኝነታችሁን አውቃችሁ በቅዱሱ እግዚአብሔር ስትወቀሱ፣ እና መማለጫ የሚባል ነገር ሲጠፋ፣ ሥጋ የለበሰው የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የእኛን ኑሮ እንደኖረ፣ እኛ ልንሞት የተገባንን ሞት እንደሞተ፣ ፍጹም የሆነውን ኑሮ ኖሮ እስከ መስቀል ሞት ድረስ ታዛዥነቱን እንዳሳየ እና ለሚያምኑም ሁሉ የእግዚአብሔር ፍጹም ሕይወት እንደተዘጋጀ የሚገልጽ ነው። ከዚያም እንዲህ ተብሎ ሊጠየቅ ይችላል፡- "ያን ፍጹም ሕይወት ለማግኘት ምን ማድረግ ይገባል?" መልሱም ይህ ነው፡- "ምንም! በቃ የሚያስፈልገው ማመን ብቻ ነው። በእምነት የመጣ ባዶ እጅ ይህን ሕይወት ይወስዳል።" ከዚያም ማብራሪያው ይቀጥላል፡- "በተመሳሳይ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለው ሊቀድሰን ነው። ከዚያ ወዲያ ምን ልታደርጉ ትፈልጋላችሁ?

የሚፈለገው በቃ ማመን ብቻ ነው፡፡ እምነት ለማጽደቅ እንደሚሠራው ሁሉ ለመቀደስም የሚሠራው እንዲህ ነው፡፡

እንደተዋጁ ወንዶች እና ሴቶች በእነዚህ አካላዊ ውርሶቻችን ሆን ብሎ ሕሊናዊ ተሳትፎ የማድረጉ አጠቃላይ ጽንሰ-ሃሳቦች ውስጥ በሂሳብ ስሌት እንደ ጋራ አብዝ ሆኖ የመደባለቁ ወይ ደግሞ የመቃረኑ ችግር ምን ይሆን?

(ሀ). መጽሐፍ ቅዱሳችን እንደሚለው መፈጸም የሚገባንን ተልዕኮ እንድንፈጽም ሁሉንም አካላዊ ውርሶቻችን እግዚአብሔር የመፈለጉን እውነት ይላሉ፤

“በላይ ያለውን አስቡ…” (ቆላ. 3፡2)፡፡ ይህን እንዲያደርግ የሚጠበቀው ማነው? - እናንተ ወይስ እግዚአብሔር? ኢየሱስስ “ቀኝ እጅህ ቢበድልህ፣ … በአንተ በሚኖረው በክርስቶስ አምነህ አበስብሰህ ጣለው” ብሏል እንዴ? አላለም! “ቀኝ እጅህ ብታሰናክልህ ቆርጠህ ከአንተ ጣላት” ነው ያለው (ማቴ. 5፡30)፡፡ ማድረግ አለብህ! መልዕክቱ ደርሰሃል፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስም “ነገር ግን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየነሰምሁ አስገዛዋለሁ” ብሏል (1ኛ ቆሮ. 9፡27)፡፡ በእኔ

የሚኖረው ክርስቶስ ነው ያደረገው አለን እንዴ? አላለም! “… ራሳችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ፥… ብልቶቻችሁንም የጽድቅ የጦር እቃ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ” (ሮሜ. 6፡13)። ማድረግ አለባችሁ! የሰውነታችንን እና የአእምሮአችንን ክፍሎች የሚመለከቱ ብዙ ጥቅሶችን መጥቀስ እንችላለን፤ ለምሳሌ “ከዝሙት ሽሹ” የሚለውን። ከዝሙት እንዴት መሸሽ ይቻላል? እግዚአብሔር እንደሚለው ከዝሙት መሸሽ ምርጡ መንገድ እግርን መጠቀም ነው።

(ለ). በመንፈስ የሰውነትን ሥራ መግደል የእኛ ኃላፊነት ነው

ቅዱስ ጳውሎስም የሚለው ይህንኑ ነው፡- “በመንፈስ ግን የሰውነትን ሥራ ብትገድሉ በሕይወት ትኖራላችሁ” (ሮሜ. 8፡13)። መጽሐፍ ቅዱስ የክርስቲያን ጸጋዎችን በበጎ ኮትኩቶ ስለማሳደግ በሚገልጸው ሁሉ የሚያሳየን ነገር ቢኖር መኮትኮታችን የኛ ኃላፊነት መሆኑን ነው፤ ለምሳሌ፣ “ስለዚህም ምክንያት ትጋትን ሁሉ እያሳያችሁ በእምነታችሁ ላይ በጎነትን ጨምሩ፥” (2ኛ ጴጥ. 1፡5)፤ ስለዚህ እናንተ እኔ ፍቅራችንን እና እምሮአችንን በላይ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ማሳረፍ አለብን። “በእርሱ እኖራለሁ የሚል እርሱ እንደተመላለሰ ራሱ ደግሞ ሊመላለስ ይገባዋል”

(1ኛ ዮሐ. 2፡6)፡፡ በመንፈስ ልንመላለስ ይገባናል (ገላ. 5፡6)፡፡ የክርስቶስን ዱካ መከተል አለብን (1ኛ ጴጥ. 2፡21)፡፡ ጸጋን የመኮትኮት እና የማሳደግ በጎ ሥራ የአካሎቻችንን ሁሉ ተሳትፎ ይጠይቃል፡፡

የክርስትና ሕይወት ጉልህ መገለጫዎቹ የውትድርና እና የሩጫ ሕይወት ዘርፎች ናቸው፡፡

ይህ በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ተጠቅሶ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ አንደኛው ግን ትምህርቱን ፍጹም ትክክል በሆነ መንገድ ያሳየናል፤ ከእነዚህ ሁሉ ደግሞ እጅግ የበለጠ ደጋፊ የሚባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ግን ይህ ነው፡- ፊል. 2፡12፣ “ስለዚህ፥ ወዳጆቼ ሆይ፥ ሁልጊዜ እንደታዘዛችሁ [ልብ አድርጉ፤ ክርስቶስ ሁልጊዜም ሕይወቱን በእናንተ ስለሚገልት አላለም]፥ በእናንተ ዘንድ በመኖሬ ብቻ ሳይሆን ይልቁን አሁን ስርቅ፥ በፍርሃት እና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ…” ::

በዚህ ውስጥ መሠረታዊ አስተምህሮውን አስተውሉ፡፡ አስፈላጊው ነገር ይህ ነው፡- “...የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ”፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ “ለማግኘት ሥሩ አላለም”፡፡ ምህረት የተደረገላቸው ሰዎች ናቸው፡፡ ፍጻሜውን እውን ለማድረግ መሥራት አለባቸው፤ በክርስቶስ የተሰጣቸውን እና የእነርሱ የሆነውን መዳን ለመፈጸም መትጋት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ደግሞም በፍርሃት እና በመንቀጥቀጥ መፈጸምም ይገባቸዋል፡፡ ያም የእግዚአብሔር ዓይኖች በእነርሱ ላይ እንደሆነ በመረዳት እና ሥራውም በቀላሉ የማይታይ መሆኑን (ቀልድ አለመሆኑን) በመገንዘብም መሆን አለበት፡፡ እንዲህ የሚባለው ለምንድነው? “ስለበጉ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና” (ቁጥር 13)፡፡ የእግዚአብሔር የጸጋው ሥራ መዳኔን በፍርሃት እና በመንቀጥቀጥ ለማድረግ እንድፈቅድም እንዳደርግም ያደርገኛል፡፡

ስለዚህ፣ ይህ ማለት የሚፈጽመው እግዚአብሔር ነው? ወይስ እኔ ነኝ? የእርሱ መፈጸም እና የእኔ መፈጸም በአንድ ላይ - በጋራ የሚሆኑ እውነታዎች ናቸው። የእርሱ መፈጸም በእኔ መፈጸም ይገለጣል፤ የእኔም

መፈጸምም የእርሱ መፈጸም ማስረገጫ ነው፡፡ የዚህ አሠራር ውበት ይታያችኋል? እርሱ በእኔ ከሚሠራው እኔ የምሠራው ይበልጣል ብዬ መፍራት አይገባኝም፡፡ የእኛ “መፈጸም” የእግዚአብሔርን “በእኔ መፈጸም” ቀድዶ አይጥለውም፡፡

ሌላው በፊልጵስዩስ መልዕክት ላይ ያለው ክፍል እንዲህ የሚል ጭብጥ አለው፡- “ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን (ማድረግ) እችላለሁ” (ፊል. 4፡13)፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ የሚለው ይህን ነው፡- “(ማድረግ) እችላለሁ፡፡” ሐዋርያው ምን ያክል ማድረግ ትችላለህ? ለሚለውም የሚመልሰው እንዲህ ነው፡- “ሁሉን”፡፡ በዚህ አውድ፣ “ሁሉን” የሚለው ቃል የሚያመላክተው በእግዚአብሔር ጥበቃና አቅርቦት አስፈላጊ የሆነውን ነገርን ሁሉ መፈጸምን ነው፡፡ ሐዋርያው እንደሚለው፣ “በጎደለኝ ጊዜ፣ አንዳንድ ጊዜ ሲርበኝ እና የሆዴ የረሃብ ስሜት የጀርባ አጥንቴን እስኪሰማኝ ሲደርስም ሃሴት ማድረግን እማራለሁ፡፡ በበዛልኝና በተረፈኝ ጊዜም፣ በብዙ ስለተባረክሁ ቅብጠት ድንበር እደርስ ይሆን የሚለውንም የማስተውልበት ነው፡፡ ነገር ግን፣ ሐዋርያው ንግግሩን በመቀጠል “በማጣቴ መዋረድን ብማርም፣ ከእግዚአብሔር ሃሳብ ጋር ብጣበቅም፣ ሁሉን ማድረግ እችላለሁ”፡፡ “አደርጋለሁ፤ ነገር ግን፣ ኃይልን በሚሰጠኝ

በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ”። “ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ …” የሐዋርያው ጳውሎስን የሥጋ ሕይወት የኖረው ማነው? - ክርስቶስ ወይስ ጳውሎስ? የኖረው ጳውሎስ ነው። ራሱ ቅዱስ ጳውሎስ ምላሽ ሲሰጥም እንዲህ በማለት ነው፡- “አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው።”

4. የቀውስ ተሞክሮ የለውም

በክርስቲያናዊ የሕይወት ኑሮ ውስጥ እንደ አስፈላጊ አላባ (ቁም-ነገር) ቃል የተገባ ወይም የታዘዘ የቀውስ ተሞክሮ የለም።

ስለክርስቲያናዊ ሕይወት የሚቀርቡ አንዳንድ ትምህርቶች ከዳግም መወለድ በኋላ ወይም ቢያንስ ከለውጡ እና በእውቀት ክርስትናን ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ የቀውስ ተሞክሮ የሌለው ሰው የክርስትና ሕይወቱም ተሞክሮ ዝቅተኛ እንደሆነ ይገልጻሉ። “ዘመን ተሻጋሪ

የዌስሊያውያን ፍጹማዊነት" ልንለው የምንችለው ነገር አለ፤ ይህም በማዕከላዊነት በቅድስና እና በሚያነጻ የእሳት ጥምቀት ላይ ወይም ወደ ወደ ፍጹም ፍቅር መድረስ ላይ የሚያተኩር አስተምህሮ ነው። አስተምህሮው ለአገልግሎት በሚያስፈልግ ኃይል ላይ ወይም በውስጣዊ ስሜት ላይ ብዙም አያተኩርም፤ ከዚያ ይልቅ ትምህርቱ በሰው ውስጥ መስጎ ስለላው እና በተቃርኖ ስለሚቆመው የኃጢአት መነሳሻ ሃሳብ እና ዓላማዎቹ ስለሚያስከትሉት የቀውስ ተሞክሮ ይናገራል። ስለዘመን ተሻጋሪው የዌስሊያውያን ሥነ-መለኮታዊ ትምህርት ምናልባት ዌስሊ ያስተማረው አማራጭ ሃሳብ ይኖር እንደሆነ በሚል በርዕሰ - ጉዳዩ ላይ በበቂ ሁኔታ አንብቤአለሁ። ሆኖም ባጠቃላይ ገለጻ፣ በእኔ እምነት፣ ይህ የዌስሊያውያንን ጥንታዊ ፍጹማዊነት አስተምህሮ ትክክለኛ ወኪል ሃሳብ ነው።

"ጥንታዊ ጴንጤቆስጤያዊ" አስተምህሮም አለ፤ ይህም ለመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አጽንዖት የሚሰጥ ሲሆን፣ ተለዋጭነት በሌለው መንገድ ከዳግም ውልደት በኋላ የሚሆን እና በልሳን ንግግር የሚገለጥ ነው፤ የዚህን የኃይል ጥምቀት የምታውቁበት ሁኔታም (ወደ እናንት በመጣ ጊዜ) ልሳንን

ትናገራላችሁ፡፡ ጥንታዊው የጴንጤቆስጤ እምነት ማዕከላዊ ትኩረት ለአገልግሎት ኃይል የማስፈለጉ ጉዳይ ነው፡፡

በሦስተኝነትም፣ ዘመናዊው “መነቃቃት ንቅናቄ” ይጠቀሳል፡፡ ልክ እንደ ዘመን-ተሻጋሪው የጴንጤቆስጤ እንቅስቃሴ፣ የዘመናዊው ጴንጤቆስጤ አስተማሪዎች የቀውስን ተሞክሮ አስፈላጊነት ደግፎ ለመስበክ የጥንቶቹ ይጠቅሱ የነበሩትን የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ክፍሎች ይጠቅሷቸዋል፡፡ በብዙ አጋጣሚዎችም እነዚህ ሰባኪዎች (በእርግጥ ዘመናዊዎቹ የተለያየ ዓይነት አስተሳሰብ ቢኖርም)፣ አዲስ ልሳንን እንዲነገር በመስበክ ረገድ አጽንኦት ይሰጣሉ፡፡ አንዳንዶቹ “ቅዱስ ሳቅ” የሳቃቸሁበት ሁኔታ ከተፈጠረ፣ እንደ “በቂ” እና አርኪ የክርስትና ጉዞ ጅማሬ ይቆጥሩታል፡፡ አንዳንዶች በሌላ በኩል፣ በልሳን መናገር የተሳናችሁ እንደሆነ እንደ አንዳች ሥነ-ልቦናዊ እክል ይወስዱታል፤ ይህ እክል እንደተወገደም ልሳኑ እንደሚገለጥ ያምናሉ፡፡ በእነዚህኛዎቹ ዘንድ አጽንዖቱ (እንደ ዘመን ተሻጋሪው የዌስሊያውያን የፍጽምና እምነት) ወይም ደግሞ (እንደ ጥንቱ ጴንጤቆስጤ እምነት) በሚያነጻው መንፈስ ጥምቀት ላይ አይደለም፤ ከዚያ ይልቅ፣ ሃሴት-የተሞላው ጥምቀት ላይ ነው ትኩረቱ፡፡ እየተናገርኩ ያለሁት ጠቅለል ያለውን ነገር ቢሆንም፣ ትክክል እንደሆነ ነው የማምነው፡፡

በአራትኝነት፣ የተለያዩ ዓይነት እና ቅርጽ ያላቸው “ከፍተኛ የሕይወት ደረጃ”ን የሚሳዩ ትምህርቶች አሉ። እነዚህ ትምህርቶች በጋራ የሚይዙትም ይህን ነው፡- “በቃ፣ ተለውጠሃል፤ በቃ ለክርስቶስ አንድ ሆነሃል፤ በቃ ዳግም ተወልደሃል፤ እና ለቀውስ እና ለእምነት ራስህን ሰጥተሃል፤ በዚህም ራስህን ጥለህ ለእግዚአብሔር መገለጥ የምትፈቅድበት ነው፤ ለክርስቶስም ራስህን የተመቸ የምታደርግበት ነው። የጋራ መግባቢያውም እንደ ልሳን፣ ወይም ቅዱስ ሳቅ፣ አለያም ቅዱስ ጩኸት ወይም ዝላይ ባለ ያለውጫዊ መገለጥ፤ ነገር ግን የመጨረሻ ውጤቱ ቅዱስ ሕይወት ለመኖር አዲስ ኃይል መገኘቱ ሲሆን ትኩረቱም በቅድስና ላይ የበለጠ ብቁ በመሆን መንገድ ይሆናል።

በአምስተኝነት፣ ጥንታዊም ሆነ ዘመናዊ ተሟጋቾች ያሉት ትምህርትም አለ። በማረጋገጫ ላይ ትኩረት የሚያደርግ እና “የመንፈስ ቅዱስ ማኅተም” በሚል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቋንቋ የሚገለጥ ነው። ከለውጥ አራማጆቹ መካከልም ቶማስ ጉድዊን ለምሳሌ ይህንኑ አስተምሯል። በእኛም ዘመን በዚህ አስተሳሰብ ላይ የጸና እምነት ያላቸውና ሃሳቡንም

በአጽንኦት እየደጋገሙ የሚገልጹ የተወሰኑ ሰባኪዎችም አሉ፡፡ የዚህ አስተምህሮ መሠረታዊ ትኩረትም፣ ከዳግም ልደት እና ከለውጥ በኋላ፣ አማኙ አዲስ ወደሆነ ሕይወት ሲገባና የመንፈስ ቅዱስን ማኅተም በማረጋገጫነት ሲቀበል (አንዳንዶች የመንፈስ ቅዱስ ማኅተም እና ጥምቀት አንድነቱን ይናገራሉ) ተከትሎት የቀውስ ተሞክሮ ውስጥ ይገባል በሚለው ላይ ነው፡፡ ይህም በውጤቱ፣ በአማኙ ሕይወት አዲስ መንፈሳዊ ምስክርነት ያለው ኃይል እና ጉልበት የሚከሰት ነው፤ በዚህ ሰው ውስጥ አንገብጋቢ ሆኖ የሚመጣ ነገር ቢኖር፣ የእርሱ ጠቀሜታ የሚገለጠው ከመንፈስ ቅዱስ ማኅተም በኋላ መሆኑ ነው፡፡

ከላይ የተገለጹት አምስቱ የአስተምህሮ አቋሞች ናቸው፤ እነዚህም ሁሉ ታዲያ በውስጣቸው ንዑሳን አስተምህሮችን የቀያዙ ናቸው፡፡ ሆኖም እነዚህ በዋናነት ለውጥን እና ዳግም ልደትን ተከትሎ የቀውስ ተሞክሮ የመከሰቱን ነገር የሚያስተምሩ ሲሆን፣ አንዳንዶቹ ይህ የቃል መፈጸም መሆኑን ሲገልጹ ሌሎች ደግሞ ትዕዛዝ እና ክርስቲያናዊ ሕይወትን በመኖር ውስጥ ዋና ነገር መሆኑን ያሰምሩበታል፡፡

በነዚህ ትምህርቶች ውስጥ የጋራ ነጥባቸው ምንድነው?

(ነ) ዳግም ልደት እና ለውጥ (አንዳንዶች ለውጥ ብቻ ነው ይሉታል) ብቻ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ጤናማ የክርስትና ሕይወት ለመምራት ገና በትክክል እንዳልተሰናዳ የሚያሳይ ነው፡፡ አስተምህሮው እንዲህ የሚል ነው፡- “አሁን አንተ ክርስቲያን ነህ፤ ድነሃል፡፡ የመንፈስ ቅዱስ መኖሪያም ሆነሃል፡፡ መልካም! ነገር ግን፣ በእርግጥም ሕይወትህን በእውነት የምትኖር ከሆነ፣ ኃይልን በተሞላ ሁኔታ፣ በአሸናፊ ጸጋ የምትገለጥ ከሆነ፣ የሚረባ ሕይወት የምትመራ ከሆነ፣ ምስክርነትህን ጠብቀህ የምትሄድ ከሆነ፣ በዚህ ከፍታ የምትጓዝ ከሆነ፣ ክብር እና ውበትን የምትጠብቅ ከሆነ፣ እድገትህን የምታዘልቅ ከሆነ፣ የእግዚአብሔር ጸጋ ልምምድ አለህ ማለት ነው፡፡ አዎ፣ ተለውጠሃል፤ እንስማማለን፤ ይሁን እንጂ፣ ወደሌላ ተሞክሮ ካልገባህ በስተቀር ይሄ ብቻውን በእውነት ልዩ አያደርግህም፡፡ ለውጥ እና ዳግም ልደት ለሞት ብቁ ያደርጉሃል፤ ሆኖም ለመኖር ግን አያስታጥቁህም፡፡ ለመኖር ከፈለግህ፣ የቀውስ ተሞክሮ ያስፈልግሃል፡፡

(2) ከዳግም ውልደት በኋላ ያለው ተሞክሮ የተወሰኑ ነገሮችን በማሟላት የሚፈለግ እና የሚገኝ ወይም የተወሰኑ ነገሮችን በመጠቀም የሚደረስበት ነው።።

በዚህ ረገድ የተለያየ ትምህርት የሚያስተምሩ ወገኖች እንደሚሉት ተሞክሮው ሳይፈለግ የሚመጣ ነው፤ ነገር ግን፣ ነገሩ የሚጠይቀውን በመሆንም የሚከሰት ነው።። እንዲህ ያለውን ተሞክሮ ለማግኘት መፈለግ፣ በፍለጋው ውስጥም የተወሰኑ መሥፈርቶችን ማሟላት ያስፈልጋል።። እያንዳንዱ አስተሳሰብ የራሱ የሆኑ ማሟላት የሚገባው ሁኔታዎች አሉት፤ በእነዚያ ሁኔታዎች ውስጥ ሌሎች ልዩ ልዩ ሁኔታዎችም ይኖራሉ፤ ሆኖም የእነዚህ ሁኔታዎች የጋራ ጉዳይ ቢኖር የተወሰኑ ሁኔታዎችን በማሟላት ተሞክሮው እስኪገኝ ድረስ የመፈለጉ እውነት ነው።።

(3) የኋለኛው ተሞክሮ ያላቸው አማኞች ሁሉ ይህን ያውቁታል፤ ምክንያቱም ይህ በክርስቲያን ሕሊና ውስጥ ተመዝግቦ የሚቆይ ስለሆነ።። በጣም በወረደ አስተምህሮ ሰው ወደ ንስሃ እና ወደ እምነት ሊመጣ ይችላል።። በእምነት የደከመው ሰው የቃል ኪዳኑን አማኝ በያዘበት እና አዳኝነቱን

ባመነበት ቅጽበት፣ መጥራትም ሆነ ማጽደቅ የእግዚአብሔር ሕጋዊ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ ለወንድም ሆነ ለሴት፣ ሐዋርያው ጳውሎስ ተትረፍርፎ እንደጸደቀ፣ አገስቲን የተባለውም አማኝ ይህንኑ ጽድቅ እንደተቀበለ ፍጹም መጽደቅ የሚቻል ነገር ነው፤ ነገር ግን ይህን አለማወቅ ከተብራራ ትምህርት እጥረት መሆን አለበት፡፡ የቀውስ ሥነ-መለኮት አቀንቃኞች ሁሉ ግን እንደዚያ አለመሆኑን ይገልጻሉ፡፡ ተሞክሮው ያለው ሁሉ ያውቀዋል፤ ምክንያቱም ይህ በሁሉ ሕሊና ውስጥ ተጽፎአል፡፡

አሁን በዚህ ደረጃ የጥንቶቹ ጴንጤቆስጤዎች አማኝ ለውጡን የሚረዳበት ግልጽ መሥፈርት ያውም ልሳን መናገር ነው በማለታቸው ብዙም ከፉ አይባሉም፤ ምክንያቱም ሌሎች በአስተምህሮ ክፉ የሚባሉ አሉና፤ ይህንኑ የመዳን መንገድ የሚያስተምሩቱ፣ ግን ደግሞ ለድነታቸው ማስረገጫ ምንም ዓይነት መስፈርቶቸን የማያስቀምቱ ከቃላት በላይ የከፉ ናቸው፡፡ ስለዚህም ሰዎች “እኔ ይህ ተሞክሮ ሊኖረኝ ይገባል፤ ያለዚህ ተሞክሮ ተራ ክርስቲያን የምሆን ከሆነ፣ ይህ እስኪኖረኝ ድረስ በእርግጥ ክርስቲያን አልባልም፡፡ ይህ ሲኖረኝ እንዴት አውቃለሁ? የሁሉም አስተሳሰቦች

መሠረታዊ ምላሽ ግን በውስጥህ ታውቀዋለህ፤ ምክንያቱም በሕሊናህ የተጻፈ - የሚገለጥ ነው የሚል ነው።።

(4) ከዚህ አስተምህሮ በስተጀርባ የተመረጡ እና ጥያቄ ፈጣሪ የተወሰኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አጠቃቀም አለ።። በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንደተመሠረቱ እና የመጽሐፍ ቅዱስን ቋንቋ የሚጠቅሱ የቀውስ አስተምህሮዎች ሁሉ ተሞክሮውን ይይዛሉ።። ለምሳሌ፣ በጥንታውያኑ ዌስሊያውያን የፍጹማዊነት ጽንሰ-ሃሳብ የድነት መመዘኛው እና መለኪያው እንዲሁም መፈተኛው "የልብ ንጽሕና" ነው፤ ይህም ከሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ 15፡9 "ልባቸውንም በእምነት ሲያነጻ..." ከሚለው የተወሰደ ነው።። ሆኖም ይህ ዐውድ፣ እየተናገረ ያለው ስለጸጋ ሁለተኛ (ሰልባጅ) ሥራ አይደለም፤ ይልቁንም በቆርኖሊዮስ እና በወዳጆቹ ልብ እየሠራ ያለው አንደኛ የሆነው የእግዚአብሔር ጸጋ መሆኑ ነው የተመላከተው።። የአጠቃላይ ቅድስና ሃሳብም የተወሰደው ከ1ኛ የተሰሎንቄ መልዕክት ነው፡- "የሰላምም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤ መንፈሳችሁም ነፍሳችሁም ሥጋችሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ያለነቀፋ ፈጽመው ይጠበቁ" (1ኛ ተሰ. 5፡23)።። "የኢየሱስ ክርስቶስን የማዳን

ሕይወት” የሚለው ሃሳብ በአንዳንድ ትምህርቶች “ከፍ ያለ ደረጃ” በጣም የታወቀ ገለጻ ነው። የተወሰደውም ከሮሜ 5፡10 ነው፡- “ጠላቶች ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን፥ ይልቁንም ከታረቅን በኋላ በሕይወቱ እንድናለን”። በቀውስ በኩል ራስን ዝቅ አድርጎ በማለፍ ስለሚገኝ የድል ሕይወት የሚያስተምረው ሥነ-መለኮት የሚመራው በዚያ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሲሆን፣ ቀጥሎም ወደዚህ ሃሳብ ይስፈነጠራል፤ “የክርስቶስ የማዳን ሕይወት” ወደሚል።

ስለዚህ፣ በእነዚህ የክርስቲያናዊ ሕይወት የቀውስ ሥነ-መለኮታዊ ሃሳቦች ውስጥ የጋራ ሃሳብ ሆኖ የሚታየው አስተምህሮው በጣም ተመረጠ እና ጥያቄ ፈጣሪ በሆነ መንገድ የተወሰኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን መጠቀም ነው።

ይህ አስተምህሮ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንዳልሆነ እንዴት ማወቅ እንችላለን?

በአዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት አንድም ክርስቲያን አማኝ ወይም ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ለተከሰተ ችግር የቀውስ ተሞክሮን መፈለግን እንደመፍትሄ ስለማቅረቡ የምናገኘው ፍንጭ የለም።

(1.) የክፍፍልን ችግር አስቡ። በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የቡድን ክፍፍል መንፈስ ነበር። አንድ ቀን ለሐዋርያው ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን አካባቢ እየሆነ ያለውን ነገር በመንገር ቅዱስ ሃሜት አማ - ያም የቀሎዔ ቤተሰብ ነው፤ "ወንድሞቼ ሆይ፥ በመካከላችሁ ክርክር እንዳለ ስለ እናንተ የቀሎዔ ቤተ ሰዎች አስታውቀውኛልና" በማለት ሐዋርያው ነገሩን ጠቁሟል (1ኛ ቆሮ. 1፡11)። ሐዋርያው የክርክሩን አካሄድ ሁኔታም ገልጾአል። በቡድን የተከፋፈለ መንፈስ ውስጥ ከገቡ አማኞች በላይ ማን ሥጋዊ ሊባል ይችላል? እነዚህ አማኞች "በአንዱ መንፈስ የተጠመቁ እና አንድ አካል ለመሆን ከአንዱ መንፈስ የጠጡ" (1ኛ ቆሮ. 12፡13)ናቸው። እነዚህ አማኞች በመንፈስ ቅዱስ አንድ ዓይነት ልምምድ የነበራቸው ናቸው። ሁለት ደረጃ ያላቸው ክርስቲያኖች አልነበሩም፤ ክርስቶስን አምነው የተለወጡ እና በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁ ናቸው፤ የተለወጡ እና ወደ

ክርስቶስ ሕይወት ከፍታ የገቡ ናቸው፤ ክርስቲያን የሆኑ እና በመንፈስ ቅዱስ እሳት የተጠመቁም ናቸው፡፡ በእነዚህ ክርስቲያኖች ዘንድ የደረጃ እና የመደብ ክፍፍል እንደነበረ በመልዕክቱ ውስጥ ምንም ዓይነት ፍንጭ የለም፡፡ ለዚህም ነው ሐዋርያው ለቤተ ክርስቲያኒቱ በጻፈው ደብዳቤ “በክርስቶስ ኢየሱስ ለተቀደሱት፥” ያለው፡፡ እንዲሁም ሃሳቡን ይቀጥልና፣ በመካከላቸው ክፍፍል እና መቦዳደን እንዳለ ይነግራቸዋል፤ በዚህም አንዳንዶቹ ራሳቸውን የጳውሎስ፣ ሌሎቹ የኬፋ - ማለትም የጴጥሮስ፣ እንዲሁም ራሳቸውን መንፈሳዊ ያደረጉ ሌሎች ደግሞ “እኛ ክርስቲያኖች ነን፤ እኛ የክርስቶስ ብቻ ነን” ብለው ነበር፡፡ ሐዋርያው ጳወሎስ ግን ሁሉንም በአንድ ማሰሮ - በአንድ ክፍል ውስጥ ነው ያስቀመጣቸው፡፡

ሐዋርያው ይህን ጉዳይ ያስተናገደው እንዴት ነው? የዚህ ሁሉ ክፍፍል ምክንያት በመንፈስ ቅዱስ በፍጹም ያለመጠመቃቸው ማስረገጫ አድርጎ እንደተቀበለው ተናግሮ ይሆን? ከውርስ ኃጢአት በፍጹም መንጻት ሲገባቸው በመጣበቃቸው እንደሆነ ገልጾ ይሆን? ለዚህ ሥር-ለሰደደ እና ተስፋፊ ለሆነ የመቧደን እና የመከፋፈል በሽታ ሐዋርያው ጳውሎስ እንደ መድኃኒት ያቀረበላቸው ነገር ምንድን ነው? የበለጠ ነገር እንዲያገኙ

በጀመሩት መንገድ እንዲቀጥሉ አልነገራቸውም። ከዚያ ይልቅ በእውነት ወደሆኑት እና ወዳላቸው እውነት እንዲመጡ እና ከእውነቱ ጋር እንዲጣበቁ ነው በምክሩ ግድ ያላቸው። እንዲህ በማለት፡- “ክርስቶስ ተከፍሎአልን? ጳውሎስስ ስለእናንተ ተሰቀለን?” ይህንንም በማለት ቀድመው ወደሆኑት እና ወዳላቸው እውነት እንዲመጡ ነው መንገደ ያሳያቸው። እነርሱ ያላቸውን እና የሆኑትን ሲገነዘቡ እና ወደዚያ እውነት ሲመጡ መከፋፈሉ ተጠርጎ ይጠፋል። ልዩነቱን አያችሁ? የበለጠ ነገር ማግኘት አለባችሁ አላላቸውም፤ ያላቸው እንዲህ ነው፡- “በክርስቶስ የእናንተ የሆነውን መገንዘብ እና ከዚያ እውነት ጋር መስማማት አለባችሁ”።

(2) የሥነ-ምግባር ችግር፡- የሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክት በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን አንዳንድ አማኞች በአመንዝራነት ውስጥ ተዘፍቀው እንደነበር ይገልጻል። እነዚህ ሰዎች በአስደንጋጭ ሁኔታ በጣም በወረደ የሥነ-ምግባር ዝቅጠት ውስጥ ገብተው ነበር። የሚያስፈልግ ከሆነም፣ ከውርስ ታጢአት ለመውጣት የመንፈስ ቅዱስ እሳት ጥምቀት አስፈልጓቸዋል። ክርስቲያኖች ከሴተኛ አዳሪዎች ጋር ሳይቀር ይወጡ

ነበር፤ በተለይም ደግሞ በቤተ አምልኮ ውስጥ ለማመንዘር ከተዘጋጁ ሴቶች ጋር ሳይቀር ይተኙም ነበር፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ለዚህ ከባድ ችግር የሰጠው ምላሽ ምን ነበር ታዲያ? “መብል ለሆድ ነው፥ ሆድም ለመብል ነው፤ እግዚአብሔር ግን ይህንም ያንም ያጠፋቸዋል። ሥጋ ግን ለጌታ ነው እንጂ ለዝሙት አይደለም፤ ጌታም ለሥጋ ነው፤ እግዚአብሔርም ጌታንም አስነሣ እኛንም በኃይሉ ያስነሣናል። ሥጋችሁ የክርስቶስ ብልቶች እንደ ሆነ አታውቁምን? እንግዲህ የክርስቶስን ብልቶች ወስጄ የጋለሞታ ብልቶች ላድርጋቸውን? አይገባም። ወይስ ከጋለሞታ ጋር የሚተባበር አንድ ሥጋ እንዲሆን አታውቁምን? ሁለቱ አንድ ሥጋ ይሆናሉ ተብሎአልና። ከጌታ ጋር የሚተባበር ግን አንድ መንፈስ ነው። ከዝሙት ሽሹ። ሰው የሚያደርገው ኃጢአት ሁሉ ከሥጋ ውጭ ነው፤ ዝሙትን የሚሠራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኃጢአትን ይሠራል። ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።”

ሐዋርያው ያደረገውን አያችሁ? በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን አጠቃላይ በሆነ ሁኔታ ችግር ፈጣሪና የሥነ-ምግባር ውድቀት በተመለከተ ጊዜ ጥራቱ ከፍ

ያለ የጸጋ ስጦታ እንደሚያስፈልጋቸው አልተናገረም፡፡ “ከዚህ እድፈት እና ቁሻሻ የአመንዝራነት ዝንባሌ ለመንጻት የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ያስፈልጋችኋል” አላላቸውም፡፡ እንደዚህ አላለም፡፡ በዚያ ፈንታ “...አታውቁምን? ወይም ...አታውቁም እንዴ?” ነበር ያላቸው፡፡ ማን እንደሆናችሁ አስቡ፤ ከክርስቶስ ጋር ኅብረት ለማድረግ በተጠራችሁ እና ኃጢአታችሁን ለመናዘዝ እና በእርሱ እምነት ለመጓዝ በወሰናችሁ ጊዜ፣ ምን ዓይነት ግንኙነት እንደፈጠራችሁም አስታውሱ፡፡ እውነተኛ ኅብረት ነው፡፡ “ወደ ልጁ ወደኢየሱስ ክርስቶስ ኅብረት የጠራችሁ እግዚአብሔር ታማኝ ነው፡፡ ኅብረቱ እውነተኛ እንደሆነ አታምኑምን? ከሴተኛ አዳሪ ጋር ሥጋዊ ኅብረት ለማድረግ ሲኬድ ክርስቶስን ይዞ ነው፡፡ “አታውቁምን? እንግዲህ የክርስቶስን ብልቶች ወስጄ የጋለሞታ ብልቶች ላድርጋቸውን? አይገባም። ወይስ ከጋለሞታ ጋር የሚተባበር አንድ ሥጋ እንዲሆን አታውቁምን?...አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፡፡” ክርስቶስ ኢየሱስ በመስቀል ሞት ሲሞት፣ በመስቀል ላይ ያን የመለኮትን የእሳት ቁጣ ሲታገስ፣ የሰውን ልጅ ለመግዛት ነው፡፡ ስለዚህ እጃችሁ፣ እግራችሁ፣ የሥነ-ወሲብ አካሎቻችሁ ሁሉ በእርሱ

በቅዱስ ደሙ የተገዙ ንብረቶች ናቸው፡፡ እናንተ ቆሮንቶሳውያን፣ ይህንን አትረዱም ወይ? ይህን አታውቁም ወይ?”

ሐዋርያው ጳውሎስ ታዲያ በዚህ ሁሉ ውስጥ አንድም ጊዜ እንኳ ቆሮንቶሳውያን በዚህ መልኩ የኖሩት - ያን ባሕርይ ያሳዩት የቀውስ ተሞክሮ ስላልነበራቸው እንደሆነ አልተናገረም፡፡ እርሱ ለእነርሱ ያላቸው ነገር ቢኖር፣ እነዚህን ታላላቅ ማመላከቻዎችን ነው፡- “እናንተ የክርስቶስ ናችሁ፤ እናንተ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያዎች ናችሁ፤ በዋጋ ተገዝታችኋል፡፡ የሚያስፈልጋችሁም ሌላ ተሞክሮ አይደለም፤ ያላችሁን እውነተኛ ሕይወት ገልጦ መኖር ብቻ ነው፤ የሆናችሁትንም መሆን ብቻ ነው፡፡” የመጀመሪያውን የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን መልእክት ስታነቡ የቤተ ክርስቲያኒቱን ችግሮች ሁሉ ታስተውላላችሁ፤ በዚያ ክፍል አጽንዖት ተሰጥቶት ተደጋግሞ የተገለጠው ያ ስለሆነ ማለት ነው፡፡ ይኸው አጽንዖትም በአዲስ ኪዳን የመልዕክት መጻሕፍት ሁሉ የሚታገኙት ነገር ነው፡፡

እኔ አማኞች መንፈሳዊ ቀውስ አይገጥማቸውም የሚል ነገር እያልኩ አይደለም፤ ይህን ካልኩ ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ እና ከክርስቲያኖች

ግለ-ታሪክ መጻሕፍት እውነታዎች - ከምስክርነቶች ጋር እጋጫለሁ። ክርስቲያኖች በቀውስ ውስጥ ያልፋሉ፤ ከእነዚህ ቀውሶች አንዳንዶቹ ለአጭር ጊዜ የሚከሰቱ ናቸው፤ ሆኖም እነዚህ ክስተቶች ክርስቲያኖችን ወደ አዲስ መንፈሳዊ እውነታ እና ከዚያ በፊት አይተዉት ወደማያውቁት የኃይል እውቀት የሚያመጡም ናቸው። በዚህ ጉዳይ ላይ እየተከራከርኩ አይደለም! ክርስቲያኖች ቀውስ ፈጽሞ አይገጥማቸውም ብል ራሴን አሞኛለሁ። ይሁንና እኔ እያልኩ ያለሁት መጽሐፍ ቅዱስ በየትም ቦታ ክርስቲያናዊ ሕይወትን ለማቅናት መንፈሳዊ ቀውስን እንደ አስፈላጊ ጉዳይ አያዝም ወይም የቃል ዋስትና አይሰጥም። እነዚህ ሁለት ጉዳዮች የሁለት ዓለም ሃሳቦች ናቸው። በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉም ዓይነት ችግሮች ቢያንስ በመርህ ደረጃ እንዴት ሥፍራ እንደያዙ ማየት ይቻላል፤ እነዚህም የሥነ-ምግባር ግድፈቶች፣ ማኅበራዊ ህጸፆች፣ ግለሰባዊ ውስጣዊ ችግሮች፣ ከውርስ ኃጢኣት ጋር የተገናኙ ችግሮች፣ ከሥጋ እና ከዓለም ጋር የተያያዙ ችግሮች፣ … ተጠቅሰዋል። ይሁን እንጂ፣ ሐዋርያት መልዕክቶች ለእነዚህ ችግሮች በፍጹም፣ በፍጹም፣ በፍጹም የቀውስን ተሞክሮ እንደ እግዚአብሔር መልስ አላቀረቡልንም።

እንደዚህ ከሆነ ታዲያ፣ በሐርያት ምዕራፍ 2፣ 8፣ 10 እና 19 ላይ የተጠቀሱት “አራቱ ጴንጤቆስጤዎች” የተባሉት ምንድን ናቸው? በዚህ ሥፍራ እነዚህን ምንባቦች አናብራራም፤ ይሁንና ምንባቦች ምን እንደሚያስተምሩ አምርሮ መረዳት ለፈለገ፣ “ኤ ቲዎሎጂ ኡቭ ሆሊ ስፒሪት (የመንፈስ ቅዱስ ሥነ-መለኮት)” የሚለውን “የኤፍ.ዲ. ብሩነርስን አጋዥ መጽሐፍ (Grand Rapids, 1970) እንዲያነቡ አበረታታለሁ። በብሩነርስ መጸሐፍ አንድ ወይም ሁለት ሥፍራ <u>የባርቲያን</u> የመጽሐፍ ቅዱስ ምልከታ ሠፍሯል። እኔ ይህን ምልከታ አልያዝኩም። አንዳንዶች እንደሚሉት ብሩነርስ የጥምቀት እውነታዊ ምልከታ አለው። ይህንን አንዳንዶቻችን ቅዱስ ሥርዓታዊ ምልከታ እንለዋለን። በእርግጥ ጸጋ በጥምቀት ውሃ ውስጥ ሰዎችን አግኝቷቸዋል። ነገር ግን ከእነዚህ ሁለት ድክመቶች ባሻገር፣ ብሩነርስ በእነዚያ ሐዋርያት ሥራ ክፍ ሎች ላይ ያቀረበው መንደርደሪያ ጥበብ የተሞላበት ነው። እኔ እንደገባኝ፣ እነዚያን “አራት የጴንጤቆስጤዎች” የተረጎመበትም መንገድ ጥያቄ በማይነሳበት ሁኔታ ነው።

ክርስቲያን ዛሬ በመንፈስ ቅዱስ ከተሞላው የበለጠ ነገ እንዲሞላ መጸለይ የለበትም እያልኩ አይደለም፡፡ እንደርሱ አይደለም የምለው! እኔ ክርስቲያን በዓይነቱ አስተማሪ እና ጥልቀት ያለው እና ከዛሬ ይልቅ ነገ የበለጠ ክርስቶስን ማወቅ የለበትም ብዬ ይሆን? እንደርሱ አላልኩም! ይህን ግራ አጋቢ እና ቅዠት የተሞላውን የቀውስ ትምህርት በሙሉ ኃይሌ የምቃወመውን ያክል፣ “ሁሉ አለኝ፤ አንዳች አያሻኝም” የሚለውንም የሎዶቂያን መንፈስም እቃወማለሁ፡፡ ለማለትም እንኳ ቢሆን “በክርስቶስ ሁሉ አለን፤ በዚህ እውነት ላይ እንደላደል” የሚለው ነው አሁንም በአዲስ ኪዳን ትምህርት የሚያስኬደን፡፡ ምንም እንኳ እግዚአብሔር “በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን…” ቢሆንም፣ የሕይወት ዘመናችንን በመሮጥ የምናሳልፈው የበረከቶቻችንን ጫፍ ለመያዝ ነው፡፡ ለማግኘት በጣም ተግተን የተገኘን እንደሆነ፣ የምናገኘው የዋናውን በረከት ቀብድ ነው፤ ዋናው ወደፊት ነው፡፡ እግዚአብሔር ያለመስማማትን መንፈስ ይቃወመዋል፤ “ሀብታም ነኝና ባለጠጋ ሆኜአለሁ አንድም ስንኳ አያስፈልገኝም የምትል ስለ ሆንህ፥ ጐስቋላና ምስኪንም ድሀም ዕውርም የተራቆትህም መሆንህን ስለማታውቅ፥” ይላል ጌታ “…ከአፌ ልተፋህ ነው፡፡”የእግዚአብሔርን የተትረፈረፈ የመንፈስ አቅርቦት ለማግኘት

ሳናቋረጥ ልንጸልይ ይገባናል፡፡ “አባት ከሆናችሁ ከእናንተ ከማንኛችሁም ልጁ እንጀራ ቢለምነው፥ እርሱም ድንጋይ ይሰጠዋልን? ዓሣ ደግሞ ቢለምነው በዓሣ ፋንታ እባብ ይሰጠዋልን?” (ሉቃ. ፲፩፡13) በኤፌሶን ምዕራፍ ፩ ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ የሚል ሃሳብ አስፍሯል፡- “የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ።” ከዚያም ሥላሤን ለታላቅ ስለማዳኑ የማድነቅ ሥነ-መለኮት አለ፤ ይህም አብን ስለምርጫው እና በቸርነቱ ስላዘጋጀው ጸጋው፣ ወልድን ጸጋን ስለመዋጀቱ እንዲሁም መንፈስ ቅዱስን ለቤዛ ቀን ስለማተሙ ነው፡፡ በቁጥር 15ም እንዲህ ይላል፡- ““ስለዚህ እኔ ደግሞ በእናንተ ዘንድ ስለሚሆን በጌታ በኢየሱስ ስለ ማመንና ለቅዱሳን ሁሉ ስለሚሆን መውደድ ሰምቼ፥ስለ እናንተ እያመሰገንሁ ስጸልይ ስለ እናንተ ማሳሰብን አልተውም፤ የክብር አባት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ። ይህም የልባችሁ ዓይኖች ሲበሩ የመጥራቱ ተስፋ ምን እንዲሆን በቅዱሳንም ዘንድ ያለው የርስት ክብር ባለ ጠግነት ምን እንዲሆን ለምናምን ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንዲሆን ታውቁ ዘንድ ነው፤” ሐዋርያው ንግግሩን ይቀጥልና እንዲህ ይላል፡- “ይህ ሁሉ አላችሁ፤ ነገር ግን ደግሞ የጠለቀ

እውቀት እንዲኖራችሁ እለምናለሁ፤ በክርስቶስ ያላችሁን ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ፤ ክርስቶስ በእናንተ ያለውንም ትረዱ ዘንድ" እስካሁን ያለው በቂ እንዳልሆነ ሁሉ ቅዱስ ጳውሎስ በምዕራፍ 3ም ላይ ንግግሩን ይቀጥላል፡- "...ከአብ ፊት እንበረከካለሁ" ይላል፡፡ ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ስፋቱና ርዝመቱ ከፍታውም ጥልቅነቱም ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል፥ ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ፥ እስከ እግዚአብሔርም ፍጹም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ።"

ሐዋርያው ጳውሎስ እንደሚጸልይ የሚናገረው አንዳች የመነቃቃት ልምምድ ውስጥ እንዲገቡ አይደለም፤ ሁለተኛውን የጸጋ ሥራ መገለጥ በእነርሱ ለማየት አልነበረም ትጋቱ - ጸሎቱ፤ ጸሎቱ፣ ከላይ ከገለጽኳቸው አምስት ልምምዶች ውስጥ እንዲገኙም አልነበረም፡፡ ከዚያ ይልቅ የሐርያው ጸሎት ከፍ ያለ መንፈሳዊ ብቃት፣ አቀባበል - አረዳድ እና በክርስቶስ ኢየሱስ ሙላት እንዲደርሱ ነበር፡፡

የአዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ከዳግም ውልደት እና መለወጥ በኋላ የቀውስ ተሞክሮ እንድንፈልግ ወይም ደግሞ እንደሚገጥመን አይነግሩንም፡፡ ይሁን እንጂ፣ ስለመንፈሳዊ ረሃብ፣ ጥማት፣ መመኘት፣ መለመን፣ በናፍቆት መጮኽ፣ ከልብ መፈለግ፣ ለማግኘት መዘርጋት… የጤናማ ነፍስ ባሕርያት ስለመሆናቸው ግልጽ በሆነ መንገድ ይነግሩናል፡፡

አንዳንድ ጊዜ እኔ ለማወቅ በጽኑ ጥያቄ ፈጥሮብኝ ጌታን እንዲህ ብዬ እምጠይቅበት ጊዜ አለ፤ “ጌታ ሆይ፣ እውን ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ አጽንዖት ሰዎች ሊረዱት ይችሉ ይሆን?” እንደሚመስለኝ፣ አንዳንድ ጊዜ ሰዎች በአንድ እጃቸው የቀውስን ክርስትና ብቻ እንደያዙ ይጓዛሉ፤ ወይም ደግሞ ይህን ድንዝዝ፣ ሕይወት-አልባ፣ ያልተፈተነ፣ ጣዕም-የለሽ እና ቀዝቃዛ ክርስትና ይዘው ቀስ በቀስ ይዘቅጣሉ፡፡ አሳዛኝ በሆነ ሁኔታም፣ ከዚያም ይኸው ሕይወት በጊዜ ሂደት ስያሜው “የተለወጠ” የሚል ሳቢ ስም እንዲያገኝ ያደርጉታል፡፡ ግልጹን ንገረኝ ካላችሁኝ፣ በእንዲህ ያለ አስተሳሰብ ሕይወቴን ከምመራ የቄስሊያውያኑ አስተሳሰብና ልምምድ ይሻለኛል፤ ምክንያቱም የጸጋን ሁለተኛ ሥራ ቢያስቡም፣ በእነዚህ ዘንድ

ለእግዚአብሔር እና ለእሴቶቹ ረሃብ እና መንፈሳዊ ግለት አላቸው፤ በዚህም እጃቸውን አጣጥፈው ተቀምጠው “እንዲህ ያለ ነገር የለም” ከሚሉቱ ይሻላሉ፤ ምክንያቱም እንዲህ የሚሉቱ ከቄስሊያውያኑ ጋር ሲነጻጸሩ ልባቸው እንደበረዶ የቀዘቀዘ ነው።።

5. መለኮታዊ ቅጣት

የዕብራውያን ጸሐፊ ይህን ነጥብ አሥምሮበታል፡- “እንደ ልጆችም ከእናንተ ጋር፡- ልጄ ሆይ፥ የጌታን ቅጣት አታቅልል፥ በሚገሥጽህም ጊዜ አትድከም፤ ጌታ የሚወደውን ይቀጣዋልና፥ የሚቀበለውንም ልጅ ሁሉ ይገርፈዋል ብሎ የሚነጋገረውን ምክር ረስታችኋል። ለመቀጣት ታገሡ፤ እግዚአብሔር እንደ ልጆች ያደርግላችኋልና፤ አባቱ የማይቀጣው ልጅ ማን ነው? ነገር ግን ሁሉ የቅጣት ተካፋይ ሆኖአልና ያለ ቅጣት ብትኖሩ ዲቃላዎች እንጂ ልጆች አይደላችሁም (ዕብ. 12፡5-8)።

በሰው ልጅ የመዋጀት እቅድ እና ሥራው የእግዚአብሔር ዋነኛ ዓላማ የሰውን መቀደስ እንጂ፣ ደስተኛ ማድረግ አለመሆኑን አትዘንጉ፡፡ “...አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኗልና” (ሮሜ. 8፡29)፡፡ በዚህ መንገድ ላይ ግን ብዙ ሃሴቶች - ደስታዎች አሉ፤ ይህ ክፍል እንደሚነግረን ግን “ቅጣት ሁሉ ለጊዜው የሚያሳዝን እንጂ ደስ የሚያሰኝ አይመስልም”፡፡ ከልጆቼ አንዱን “ቁንጥጫዬን” ካቀመስኩት በኋላ በአንድም አጋጣሚ በደስታ እያሸበሸበ

ማዕድ ቤቱን በደስታ መንፈስ ሲያውደው አይቼ አላውቅም። የትኛውም ጊዜው ቅጣት ደስታ ፈጣሪ አይደለም!

የተወሰነ የቀውስ ልምምድ ካለህ፣ ሠላሣ ሁለት ጥርስህ ከ24ቱ ሰዓት 27ቱንም ሰዓታት በደስታ ገጦ ታሳልፋለህ የሚለው ስብከት የተነቃቂዎቹ፣ የአነቃቂዎቹ - ማነቃቂያ እርግማን ነው! በጌታ ቅጣት ነፍሱ በምሬት ላዘነ ሰው ሰው ሠራሽ ፈገግታ ምን ይፈይድለታል? እንዲህ ላለ ሰው የማነቃቂያው ንግግር ተናጋሪ የእዮብን መካሪዎች ከመሆን አያልፍም። እንዲህ ላለ ሰው "ምን መሰለህ ወንድሜ... ያንተ ችግር፣ መንፈስ ቅዱስን አለመቀበል ነው። መንፈስ ቅዱስን ብትቀበልና በልሳን ብትናገር፣ ወደ እልፍኝህ ገብተህ ለአንድ ሰዓት በመንፈስ ቅዱስ እሳት ብትቀጣጠል፣ ለውጡን ያኔ ታየዋለህ!" ማለት ምን ይጠቅመዋል? ሰውዬው እያለፈበት ያለው ነገር እኮ ቀልድ አይደለም። የእዮብ ወዳጆች ምክር ለሰዎች በምክርነት ሲውል ታዝቤአለሁ። በንጽጽር፣ በልባችሁ መጻፍ ያለባችሁ ይህን ነው፡- "የክርስቶስን መልክ እስክንይዝ ድረስ የእግዚአብሔርን ልምጭ ግርፍ ለመቀበል መዘጋጀት ግድ ነው። "ቅጣት ሁሉ ለጊዜው የሚያሳዝን እንጂ ደስ የሚያሰኝ አይመስልም"... "ጌታ የሚወደውን

ይቀጣዋልና፥”… “እኔ የምወዳቸውን ሁሉ እገሥጻቸዋለሁ እቀጣቸውማለሁ” (ዕብ. 3፡19)፡፡ ልንገራችሁ፣ የጌታ ቅጣት የግድ በአካል ላይ የሚርፍ ልምጭ ላይሆን ይችላል፡፡ የጌታ ቅጣት በአካል ላይ በሚያርፍ የልምጭ ሕመም እና በገንዘብ ላይ በሚመጣ ከባድ ችግር ብቻ እንደሚገለጽ ፈጽሞ ማሰብ የለባችሁም፡፡ እንዲህ ያሉት ነገሮች የጌታ ቅጣት መገለጫ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል፡፡ እንደ እኔ እንደ እኔ ከጌታ ቅጦች ሁሉ የከፋ የሚለው ፊቱን ከእኛ ዘወር ባደረገ ጊዜ ነው፤ እየጸለያችሁ ኃልዎቱን ስታጡ እና ከእግዚአብሔር ጋር ጎብረት እያደረጋችሁ እንደሆነ የሚያረጋግጡላችሁን ስሜቶች ስታጡ ነው፡፡ ለእውነተኛ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ኃልዎት፣ ሃሴት ያለበትን ጎብረቱን እና ኃይል ያለውን ጸሎት እንደማጣት ምን መራር ነገር አለ? ለክርስቲያን ከዚህ የበለጠ መራር ቅጣት እኔ አላውቅም! ስለዚህ ለእውነተኛ ክርስቲያን መነገር ያለበት ነገር ይህ ነው፤ ልቡን እንዲያዳምጥ እና እንዲህ ብሎ እንዲጸልይ ማበረታታት፡-

“አቤቱ፥ እስከ መቼ ፈጽመህ ትረሳኛለህ? እስከ መቼስ ፊትህን ከእኔ ትሰውራለህ? እስከ መቼ በነፍሴ እመካከራለሁ? ትካዜስ እስከ መቼ

ሁልጊዜ ይሆናል? እስከ መቼ ጠላቴ በላዬ ይጓደዳል?አቤቱ አምላኬ፥ እየኝ ስማኝም፤ ጠላቴ፡- አሸነፍሁት እንዳይል፥ የሚያስጨንቁኝም እኔ ብናወጥ ደስ እንዳይላቸው፥ ለሞትም እንዳልተኛ ዓይኖቼን አብራ።" የመዝሙረ ዳዊት መጽሐፍ የተሞላው እንዲህ ባለው ትምህርት ነው፡፡

የእግዚብሔር ልጆች ሆይ፣ በመርህ ደረጃ በክርስቲያን ሕይወት ከእግዚአብሔር መለኮታዊ ቅጣት ማምለጫ መንገድ የለም፡፡

6. የጸጋ መንገድ

በክርስትና ሕይወት እድገት ውስጥ በእግዚአብሔር የተወሰነውን እና የተሰጠውን ጸጋ የሚተካ ሌላ ምንም ውጤታማ መንገድ የለም፡፡

እነዚህ የጸጋ መንገዶች 1ኛ. ግላዊ እንዲሁም 2ኛ. የሕዝብ ወይም ማኅበራዊ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡

1ኛ. ግላዊ፤ በግል የምንለማመዳቸው የጸጋ መንገዶች ምን እንደሆኑ እናውቃለን፡፡ ጌታችን ኢየሱስ እንዲህ ብሎ ጸልዮአል፡- “አባት ሆይ፣ ቃልህ እውነት ነው፤ በቃልህ ቀድሳቸው” (ዮሐ. 17፡17)፡፡ “ጎልማሳ መንገዱን በምን ያነጻል? ቃልህን በመጠበቅ ነው፡፡...አንተን እንዳልበድል፣ ቃልህን በልቤ ሰወርሁ” (መዝ. 119፡9፣11)፡፡ ድብቅ ጸሎት! መጸለይ፣ ምስጢራዊ እና ድንቅ፣ እና ደግሞ አስደሳች ዕድል ነው! ከመንፈሳዊ ለንቋሳነት ብዙ ምክንያቶቹ አንዱ ወሳኝ ምክንያት ይህ ነው፡- “...አትለምኑምና ለእናነት አይሆንም” (ያዕ. 4፡2)፡፡

አንዳንዶቻችሁ አድብቶ በሚጥል ኃጢአት እስካሁንም ሸባ የሆናችሁት ለምን ይመስላችኋል? ስለማትጸልዩ ከዚያ መላቀቅ አልቻላችሁም፡፡ እነዚያን አድቢ ኃጢአቶች በጸሎት በጌታ መስቀል እና በደሙ ፊት እንዲሁም በሚያነጻው በክርስቶስ መንፈስ ኃልዎት ፊት አታቀርቧቸውም፡፡ እንዲህ ለማድረግ ታማኝ እና ጽኑ ፍላጎት ያላችሁ በሆናችሁ ልክ፣ እነዚህ እንደመሸገር የተጣበቁባችሁ ኃጢአቶች ኃይላቸውን ሲያጡ እና ከላያችሁ ላይ ሲራገፉ ታያላችሁ፡፡

በክርስትና ሕይወት እድገት ውስጥ በእግዚአብሔር የተወሰነውን እና የተሰጠውን ጸጋ የሚተካ ሌላ ምንም ውጤታማ መንገድ የለም፡፡ የግል ልምምዳችሁን አጥብቃችሁ ያዙ፤ ጹሙ፤ ጸልዩ፤ የእግዚአብሔርን ቃል ለማሰላሰል ጊዜ ውሰዱ፤ ራሳችሁን እንደሚገባው መርምሩ፤ የጾም ጊዜ ወስኑ፤ የእግዚአብሔርን ፊት ለመፈለግ በቆረጣችሁበት ሁኔታ ሰውነታችሁ ለሚጠይቃችሁ እንደ ረሃብ ላለ ተገቢ ጥያቄ ተገቢ መልስ ስጡ፤ ህሊናችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም እንዲታጠብ አድርጉ፡፡ የሐዋርያው ጳውሎስን ዓላማ ዓላማችሁ አድርጉ፡- “ስለዚህ እኔ ደግሞ በእግዚአብሔር እና በሰው ፊት ሁልጊዜ ነውር የሌለባት ሕሊና ትኖረኝ ዘንድ እተጋለሁ” (ሐዋ. 24፡16)፡፡

2ኛ. የጋራ ተቋማዊ የጸጋ መንገድ፤ “በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቍረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር” (ሐዋ. 2፡42)። ኅብረት፣ ጸሎት፣ ሕይወትን መካፈል! ሰዎችን ወደ ልባችሁ - ወደ ሕይወታችሁ በማስገባት የማትፈሩበት ሥፍራ ቢኖር፣ በእግዚአብሔር ሰዎች መካከል ነው።

ኅብረት ማለት አንድ ቀን፣ በአንደ ወንበር ላይ፣ በአንድ ጣሪያ ሥር መቀመጥ ማለት አይደለም። ኅብረት ማለት ሕይወትን መካፈል ማለት ነው። “በእርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማን ነው? እንዲሁም ደግሞ ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቅም።” (1ኛ ቆሮ. 2፡11) ሸክምህን ወደ ፊት አምጥተህ ማየት የምችልበት ቦታ ካላቀረብከው እንዴት አድርጌ ልጋራህ፣ ትከሻዬን ዝቅ ላደርግልህ እና ልሸከምልህ እችላለሁ? መጽሐፍ ቅዱስ በገላትያ 6፡2 ላይ “ከእናንተ እያንዳንዱ አንዱን ሸክም ይሸከም በዚህም የክርስቶስን ሕግ ፈጽሙ” (ገላ. 6፡2)። ... “ከሚያለቅሱም ጋር አልቅሱ” (ሮሜ. 12፡15)። ታዲያ በዚህ ዓላማ ቢስ

ጠንካራ ሥጋዊ ማንነት ይዛችሁ እንደምን ይህን መፈጸም ትችላላችሁ? የእግዚአብሔርስ ቃል “ይህን ጠንካራ ማንነት እየዞራችሁ አሳዩ” የሚለውስ በየትኛው የእግዚአብሔር ቃል ክፍል ነው? ቃሉ እንደዚህ አይልም! ብዙ ክርስቲያኖች በስሜታቸው የተሰባበሩ ስለሆኑ፣ ጎብረተሰባቸው ሲያለቅስ አብረው ማልቀስ ተስኗቸው ይታያሉ፤ እነርሱም ሲያለቅሱ አብረዋቸው የሚያለቅሱ ወንድሞች እና እህቶችን ያጡ ናቸው! እንደማስበው በመጋቢነት አገልግሎቴ ውጤታማ ነገር የሆነው በድንቅ ቃላት ባጽናናሁባቸው ጊዜያቶች አይመስለኝም፤ ከዚያ ይልቅ ካዘኑ ወንድሞች እና እህቶች ጋር አዝኜ ሲያለቅሱ አብሬ ተንሰቅስቄ ባለቀስኩባቸው ወቅቶች ነው፡፡ ጎብረት ማለት ያ ነዋ!

ሃይማኖታዊነት ስለተሰማቸው ብቻ መነቃቃትን እና ተነቃቂዎችን ተከትለው የማይነጉዱ አማኞች ያሉባቸውን አብያተ ክርስቲያናት ለማየት እግዚአብሔር እንድንጸለይ ይርዳን ዘንድ እንጸልይ፡፡ እኔም ሥነ-መለኮታዊ እይታዬ ቢፈቅድልኝ እና “የተለወጠች - የተነቃቃች - ቤተ ክርስቲያን” ውስጥ ሆኜ ቢሆን ኖሮ፣ እንደእነርሱ እሮጥ ነበር፡፡ ይህን ሳስብ ግን ልክ እንደ ደጋ ብርድ ከባድ ቅዝቃዜ በአጥንቶቼ ይዘልቃል፡፡ እናንተ ባለቀሳችሁ ጊዜ የጸሎት ቤታችሁ ግድግዳ በእምባ ጎርፍ እንደሚታጠብ

እና እንቅጥቃጤ እንደሚደርስባችሁ እያሰባችሁ አታለቅሱም፡፡ በተሞክሮዬ እያላገጥኩ ወይም እያጋነንኩ አይደለም፤ እውነቱ ይኼ ስለሆነ ነው ይህን የምለው፡፡ እግዚአብሔር የሰጠን የጋራ - የጎበረት የጸጋ መንገድ ቤተ ክርስቲያን ናት፤ እርሷም የእርስ በእርስ እንክብካቤ፣ ፍቅር፣ የፍቅር ለቅሶ፣ ሃሴት፣ አንዱ አንዱን የማገልገል መንፈስ እና የወንጌል ሸክም እና ሩጫ ያለባት የእግዚአብሔር ሰዎች ውህድ አካል ናት፡፡

የግልም ሆነ የጋራ የጸጋ መንገዶች በእግዚአብሔር የተወሰኑ መንገዶች ናቸው፡፡ እነዚህን የሚተካ እና የክርስትናን ሕይወት በእውነትም ፍሬአማ ሊያደርግ የሚችል ሌላ የአገልግሎት መንገድ የለም፡፡